ኢሰመጉ ላለፉት 34 ዓመታት በቆመላቸው ዐበይት ዓላማዎች ላይ በመመርኮዝ ሁለንተናዊ፣ ሐገራዊና ሕዝባዊ ተልዕኮ በመያዝ በነደፋቸው በርካታ የመርሐ -ግብር ተግባራት አማካኝነት ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የሕግ የበላይነትና ሕጋዊ ሥርዓት እንዲሰፍንና በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲኖር የበኩሉን አስተዋጽዖ በማበርከት ላይ ይገኛል። የኢሰመጉ ዋነኛ ተግባሩ የኢትዮጵያን የሰብዓዊ መብቶችን አያያዝ ሁኔታን መከታተል፣ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በማጣራትና በመተንተን በማስረጃ የተደገፉ መግለጫዎችን ማውጣት ነው። ኢሰመጉ በሚያወጣቸው መግለጫዎች ሁሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ተጎጂዎች ፍትሕና ካሣ እንዲያገኙ፣ የጥሰት ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁና ወንጀል ሠርቶ በነጻ የመኖር ልማድ እንዲያበቃ፣ ከእያንዳንዱ ክስተት ትምህርት ተወስዶ ለወደፊቱ ጥንቃቄና ተገቢው የፖሊሲና የአፈጻጸም እርማት እንዲደረግ ሲወተውትና ሲጠይቅ ቆይቷል፣ አሁንም በመጠየቅ ላይ ነው፤ ለወደፊትም በዚሁ ይቀጥላል።

ከኢሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ክትትል ተግባራት መካከል በተለያዩ ምክንያቶች ከሚኖሩበት አካባቢ ተፈናቅለው የሚገኙ ተፈናቃዮች ያሉበትን ሁኔታ ክትትል፣ የሕግ ታራሚዎችን መብቶኘትና ሰብዓዊ መብቶቻቸው መጠበቃቸውን መከታተል፣ የፍርድ ቤቶችን ሒደት ፍትሐዊነት መከታተል ፣ በመንግሥት የወጡና የሚወጡ ሕጎችን ይዘትና አፈጻጸማቸውን ከሰብዓዊ መብቶች አንጻር መመርመር፣ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሰለባ ለሆኑ ዜጎች የተለያየ ደረጃና መልክ ያለው የሕግ ድጋፍ ይሰጣል ። በእስካሁኑ ቆይታው ኢሰመጉ 40 መደበኛ መግለጫዎችና 156 ልዩ መግለጫዎችን በተጨማሪም በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በርካታ

ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ይፋ አድርጓል። ኢሰመጉ ሁኔታና አቅም በፈቀደለት መጠን የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የሕግ የበላይነትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ካለው የጸና ዓላማ አኳያ በመሥራት ላይ ይገኛል።

1.2. የመግለጫው ወሰን

ይህ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ዘገባ ቀዳሚ ትኩረቱን የሚያደርገው ከ 2011ዓ.ም እስከ 2017 ዓ.ም ባለው ጊዜ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች በተፈጠሩ ግጭቶች በተፈናቀሉ የሃገር ወስጥ ተፈናቃዮች ላይ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል መተከል ዞን፣በአማራ ክልል ፣ በኦሮምያ ክልል እና በአፋር ክልል የተለያዩ ቦታዎች በተለያዩ የድንበር፣ የአስተዳደር መዋቅር እንዲሁም የተለያዩ ማንነትን መሰረት ባደረጉ ግጭቶች የደረሱ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን እንዲሁም ዛቻ እና ማስፈራራትን ተከትሎ የተከሰቱትን መፈናቀሎች እንዲሁም በተፈጥሯዊ ሁኔታ ምክንያት የተፈናቀሉትን ሲሆን ይህ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ዘገባ የኢሰመጉ አቅም እና የአካባቢዎቹ ነባራዊ ሁኔታ በፈቀደው ልክ በዋናነት መሠረታዊ የሚባሉትን የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች አካቶ ይዟል።

1.3. የመግለጫው ዓላማ

- የዚህ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ ዓላማ በኢትዮጵያ የተለያዩ ክልሎች በተለያዩ ጊዜ በሚነሱ ግጭቶችና የተፈጥሮ ክስተቶ ምክንያት ተፈናቅለው በተለያዩ አካባቢዎች በመጠለያና ከመጠለያ ጣቢያ ውጪ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው የሚገኙ ተፈናቃዮች ያሉበትን ሁኔታ ለመከታተል፤
- በተፈናቀሉበት ጊዜና ከተፈናቀሉ በኋላ የደረሱትን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ማጣራትና በማስረጃ አስደግፎ በማቅረብ ተገቢውን የውትወታ ስራ ለመስራት፤
- መንግስታዊም ሆነ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ተፈናቃዮች ተገቢውን ሰብዓዊ ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዲያመቻቹ ለማሳሰብ የውትወታ ስራ ለመስራት፤
- ተፈናቃዮችን መልሶ የማቋቋም እና ወደ መደበኛው ሰላማዊ ኑሯቸው እንዲመለሱ የማድረግ ስራ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ የሚገባ ጉዳይ መሆኑ በማስረጃ አስደግፎ በማቅረብ ተገቢውን የውትወታ ስራ ለመስራት ፣
- ለደረሱት ጉዳቶችና የመብት ጥሰቶች የሚመለከተው ባለድርሻ አካል በጥቃቱ የተሳተፉትን አካላት ለህግ በማቅረብ አስተማሪ ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ለማሳሰብ ነው።
- ኢሰመጉ የዚህን ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ መግለጫ ይዘትና ዓላማ በተፃረረ መልኩ፣ ከሕግና ከመልካም አስተሳሰብ ውጪ በሆነ መንገድ ማንም እንዲጠቀምበት አይፈቅድም። ይህንንም ዘገባ የሐገር ሰላምን ለማደፍረስ፣ ግለሰቦችንም ሆነ ቡድኖችን ለማጥቃት፣ ከሕግ አግባብ ውጪ ሌሎች ሲጠቀሙበት ቢገኝ ኢሰመጉ ከወዲሁ አጥብቆ ያወግዛል፣ ኃላፊነቱንም እንደማይወስድ ያሳስባል።

1.4. የክትትል ሥራው ስነ-ዘዴ

ይህ ልዩ ዘገባ የተዘጋጀው በሀገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች ከ2011ዓ.ም ጀምሮ ግጭትን መሰረት አድርገው የተፈጠሩ መፈናቀሎችን ተከትሎ በደረሱ ሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ ነው፡ ፡ ይህ ልዩ መግለጫ የተፈጠሩ ክስተቶችን የክትትል ስራዎችን በማከናወን በማስረጃ በመደገፍ ከተለያዩ ሀኃች አንጻር የተጣሱ ሰብዓዊ መብቶችን አካቶ ይዟል፡፡

ልዩ ዘገባው የተጠናቀረው ኢሰመጉ የምርመራ ባለሙያዎችን በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ማለትም በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል መተከል ዞን፣በአማራ ክልል ፣ በኦሮምያ ክልል እና በአፋር ክልል የተለያዩ ወረዳዎች በማሰማራት የምርመራ ባለሙያዎቹ በእነዚህ አካባቢዎች በተለያዩ ጊዜዎች ባደረጉት የክትትል ስራ ተደግፎ ነው፡፡ ይህ ክትትል በሚካሄድበት ወቅት ግኝቶቹን ለማረጋገጥና ለማጠናከር በቀጥታ ቃለመጠይቆች፤ ከተጎጂዎችና ከተጎጂ ቤተሰቦች፣ ከምስክሮች፣ ከሚሾ ቤተሰቦች፣ ከመንግስት እና መሳስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች አመራሮች እንዲሁም ከሌሎች ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ካላቸው አካላት ጋር ተደርገዋል፤ የቡድን ውይይቶች እና የመስክ ምልከታዎችም እንዲሁ የተገኙ መረጃዎችን ለማጠናከርና እንደ መረጃ ምንጭነትም ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ይህ የምርመራ ሂደት በሙሉ ጥብቅ የሆኑ የሰብአዊ መብት ምርመራ ስነ-ምግባር መርሆዎች የተከተለ ነው።

በተለይም በሁሉም ተሳታፊዎች በቂ መረጃ ላይ የተመሰረተ ፈቃድ የተገኘ ሲሆን፥ የምንጮችን ሚስጢራዊነት እና ደህንነት ለመጠበቅ ጥንቃቄ ተደርጓል።

በተጨማሪም ተፈናቃዮች የሚገኙበትን መጠለያ ጣቢያዎች በአካል በመገኘት ምልከታ በማድረግና በማጥናት እና ሚዛናዊነትን ለመጠበቅ የሥነድ ማስረጃዎችን ከሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች በመቀበል እና በመመርመር ለመሰብሰብ እና ለማጠናቀር ተችሏል፡፡

1.5. የክትትል ሥራው ውስንነቶች እና ያጋጠሙ ችግሮች

የዚህ ዘገባ የክትትል ሥራ በሚከናወንበት ወቅት ኢሰመጉ የሚከተሉት ዋና ዋና ውስንነቶች እና ተግዳሮቶች ኢጋጥመውታል፡-

- ኢሰመጉ ያለበት የገንዘብ፣ የሰው ኃይል፣ የድምጽና የቪዲዮ መቅረጫ እና የመሳሰሉ ለክትትል ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች እጥረት፣
- በአንዳንድ ክልሎች በነበረው የጸጥታ ስጋት ምክንያት የኢሰመጉ ባለሙያዎች እንደልብ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ ለመስራት መቸገር፣
- ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት የሚገኘው መረጃ በተመሳሳይ አቀራረብ

የማይገኝ መሆኑ፣

➢ በትግራይ ክልል ባለው የጸጥታ ችግር ምክንያት በክልሉ የሚገኙ ተፈናቃዮችን የሰብዓዊ መብት ሁኔታ ለመከታተል አለመቻል።

መነሻ ታሪክ

በዚህ ልዩ መግለጫ የተካተቱት በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል ፣በኦሮሚያ ክልል ፣ በአማራ ክልል እና በአፋር ክልል ከተለያዩ አካባቢዎች ተፈናቅለው በእነዚህ ክልሎች የሚገኙ ተፈናቃዮችን ሁኔታ ክትትል በማድረግ ግኝቶቹ እንደሚከተለው አቀርቧል፡፡

2. ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል

ኢሰመጉ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን በማንዱራ ወረዳ ገነተ ማሪያም መጠለያ፣ግልገል በለስ ፣ ቻይና ካምፕ እና በዳንጉር ወረዳ ማቡክ መጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙትን ተፈናቃዮችን ከ 13/4/2017ዓ.ም -18/4/2017ዓ.ም ጉብኝት አድርጓል፡፡

2.1. ማቡክ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በዳንጉር ወረዳ ማቡክ ከተማ አካባቢ የሚገኝ ሲሆን በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ 2,357 ሴት እና 1,982 ወንድ በድምሩ 4,339 የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ይገኛሉ፡ ፡ በመጠለያ ጣቢያው የሚገኙ ተፈናቃዮች በአካባቢያቸው በተነሳ ግጭት ምክንያት በ2014 ዓ.ም ከተለያዩ አካባቢዎች የተፈናቀሉ ሲሆን በሚኖሩበት አካባቢ ንብረት የነበራቸውና ቤተሰብ መስርተው ይኖሩ የነበሩ እና በአካባቢያቸው በተነሳ ግጭት ምክንያት ንብረታቸውንና አንዳንድ የቤተሰብ አባላቶቻቸውን አጥተዋል፡፡ አካባቢያቸውን ለቀው ወደ ከተማ በመሔድ አንድ አካባቢ የተሰበሰቡ ሲሆን እየተመዘገቡ ወደ መጠለያ ጣቢያው እንዲገቡ መደረጉን፣በመጠለያ ጣቢያው የተፈናቃይ የመኖሪያ ክፍሎች በጣም የተጨናነቀ መሆኑን፣ የፍትህ ተቋማት ለተፈናቃይ ተደራሽ በሆነ መልኩ የሚገኝ ሲሆን በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ የጸጥታና የሰላም ሁኔታን የሚቆጣጠር አካል ያለ እና አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በውይይትና በሽማግሌ የሚፈታ መሆኑን፣ ትምህርትን በተመለከተ በአካባቢው ባሉ ትምህርት ቤቶች ትምህርታቸውን እየተከታተሉ መሆኑን፣ የህክምና አገልግሎት ያለ ቢሆንም የባለሙያና የመድሀኒት እጥረት መኖሩን፣ የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ ተፈናቃዮች ወደመጠለያ ጣቢያው እንደገቡ አካባቢ ይሰጣቸው የነበረ ቢሆንም ኢሰመጉ ጉብኝት ባደረገበት ወቅት የምግብ አቅርቦት አለመኖሩን ለማወቅ ችሏል፡፡

መታወቂያ ያልተሰጣቸው በመሆኑ በአካባቢው ተንቀሳቅሰው መስራት አለመቻላቸውን፣ የፍራሽ፣ ብርድልብስ እና አንሶላ በመጠለያ ጣቢያው ሲገቡ ተሰቷቸው የነበረ መሆኑን እና ከተሰጣቸው እረጅም ጊዜ ያስቆጠረ በመሆኑ ፍራሽ፣ ብርድ ልብስና አንሶላው ያረጀ እና ለመልበስ በሚያስችል ደረጃ ላይ አለመሆኑን፣ ለሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ እንዲሁም ለጨቅላ ህጻናት የሚሆን የአልሚ ምግብ እና የቁሳቁስ አቅርቦት አለመኖሩን ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ለማወቅ ችሏል፡፡

ለመፈናቀላቸው ምክንያት የሆነው ክስተት በተፈጠረበት ወቅት ከቤተሰብ አባል በሞት ማጣታቸውን ሲያስረዱ‹‹ ወንድሜ እና የወንድሜ ልጅ በጥይት ተመተው ተገድለዋል፡፡ **ወንድሜ የ48አመት ሲሆን ግንባሩን በጥይት ተመቶ ተገድሏል፡፡ ሌላው የ 5አመቱ የወንድሜ ልጅ ደረቱን በጥይት ተመቶ ተገድሏል ሁለቱም እዚያው ተቀብረዋል**›› ብለዋል።

2.2. ግልገል በለስ 02ቀበሌ/ቻይና ካምፕ አካባቢ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በማንዱራ ወረዳ ግልገል በለስ 02 ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ ሴት-1730 ወንድ-1781 አጠቃላይ-3511 ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ተፈናቃዮች ከአማራ ክልል ጎጃም የተለያዩ ዞኖች በ 2011ዓ.ም ተፈናቅለው በመተከል ዞን ማንዱራ ወረዳ ግልገል በለስ ከተማ በ ቻይና ካምፕ መጠለያ ጣቢያ ለ3 አመት ከ 6ወር ያህል ቆይተው ወደመጡበት አካባቢ እንዲመለሱ የተደረገ ቢሆንም በ2016 ዓ.ም በተነሳ ግጭት ንብረታቸው ወድሞ፣ አንዳንዶቹም ቤተሰቦቻቸውን በሞት አጥተውና የአካል ጉዳት ደርሶባቸው በድጋሚ የተፈናቀሉ መሆኑን ገልጸውልናል፡፡ መንግስት የሰራላቸው መጠለያ ባለመኖሩ በመተከል ዞን ማንዱራ ወረዳ ግልገል በለስ ቀበሌ 02 ይኖሩ የነበሩ የአማራ ተወላጆች ተፈናቅለው ጥለውት በሄዱት ቤት ውስጥ እየኖሩ ቢሆንም የሰው ቤት በመሆኑ ልቀቁ እየተባሉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመጠለያ ጣቢያው የተፈናቃይ የመኖሪያ ክፍሎች በጣም የተጨናነቀ መሆኑን፣ የፍትህ ተቋማት ለተፈናቃይ ተደራሽ በሆነ መልኩ የሚገኝ ሲሆን የጸጥታና የሰላም ሁኔታን የሚቆጣጠር አካል ያለ እና አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በህግ የሚፈታ መሆኑን፣ ተፈናቅለው በመጡ ወቅት ለ4 ወራት የምግብ አቅርቦት የነበረ ቢሆንም ኢሰመጉ ጉብኝት ባደረገበት ወቅት የምግብ አቅርቦት አለመኖሩን ፣ የፍራሽ፣አንሶላና ብርድ ልብስ አቅርቦት አለመኖሩን፣የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ እና ለጨቅላ ህጻናት የሚሆን የተለየ ምግብና ቁሳቁስ አቅርቦት አለመኖሩን እንዲሁም የህክምና አገልግሎት አለመኖሩን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ትምህርትን በተመለከተ ድጋፍ የሚያደርግላቸው ባለመኖሩ አብዛኞቹ ህጻናት ልጆች ትምህርታቸውን ያቋረጡ ሲሆን ማስተማር የሚችሉ ቤተሰቦች በግላቸው እያስተማሩ መሆኑን እንዲሁም ልዩ ትኩረትና ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተፈናቃዮች የተለየ ድጋፍ እንደማይደረግላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ዘላቂ መፍትሄን በተመለከተ አንድ ግለሰብ **"እኔ አሁን ዳግም ወደነበርኩበት ተመልሼ ለሶስተኛ ጊዜ ቤተሰቤን ማስጨረስ አልፈልግም መንግስት እዚሁ ድጋፍ እያደረገልኝ ቦታ ተሰጥቶኝ እንደገና ሰርቼ ቤተሰቤን ማስተዳደር አፈልጋለው፡፡አሁን እኔም ቤተሰቤም የምንበላው፣ የምንጠጣው እና የምንተኛበትም የለንም ጊዜ የማይሰጥ ደድጋፍ እንፈልጋለን፣ የማብሰያ እቃዎች የሉንም፣ መታወቅያ የለንም"** በማለት ገልጸዋል፡፡

2.3. ግልገል በለስ ቀበሌ 01 መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በማንዱራ ወረዳ ግልገል በለስ 01 ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ 159 ሴት እና 160 ወንድ በድምሩ 319 ተፈናቃዮች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ተፈናቃዮች መተከል ዞን ማንዱራ ወረዳ ግልገል በለስ ቀበሌ 02 ይኖሩ የነበረ ሲሆን በግጭት ምክንያት በ 2012 ዓ.ም ተፈናቅለው 01 ቀበሌ በመሰባሰብ የአካባቢው አስተዳደር በሰራላቸው መጠለያ ጣቢያ ውስጥ ተጠልለው የቆዩ ሲሆን በመጠለያ ጣቢያው የተፈናቃይ የመኖሪያ ክፍሎች በጣም የተጨናነቀ የነበረ ሲሆን፤ ከ 1 አመት ቆይታ በኋላ የሚኖሩበት መጠለያ በመፍረሱ ከአካባቢው ማህበረሰብ

ጋር በመጠጋት ተቀላቅለው እንደሚኖሩ እና ለመፈናቀላቸውም እውቅና ባለማግኘታቸው ለበለጠ ጉዳት መዳረጋቸውን፤ የምግብ አቅርቦቱም ለ አንድ አመት ያህል ብቻ ድጋፍ ይደረግላቸው የነበረ ቢሆንም የመጠለያ ድንኳኑ ከፊረሰ በኋላ የምግብ አቅርቦቱ መቋረጡን፣ የህጻናት ትምህርትን በተመለከተ የኑሮው ሁኔታ ከእለት ወደ እለት እየተባባሰና እየከበደ የመጣ ቢሆንም አቅም ያላቸው ልጆቻቸውን በራሳቸው ጥረት በመደበኛ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ ቢሆንም መማር ያልቻሉ እና ትምህርታቸውን ያቋረጡ ብዙ ልጆች መኖራቸውን፣ ወደመጠለያ ጣቢያው በገቡ ወቅት የተመዘገቡ መሆኑን፣ በመጠለያ ጣቢያ በነበሩበት ወቅት የመጠለያ ጣቢያው ኃላፊዎች ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ከተፈናቃዮች ጋር ውይይት ያደርጉ እንደነበር፣ የፍራሽ፣ ብርድ ልብስ እና አንሶላ አቅርቦት አለመኖሩን፣ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ አለመኖሩን፣ የህክምና አገልግሎት አለመኖሩን እና ለህጻናት የተለየ የምግብ አቅርቦት አለመኖሩን ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ለማወቅ ችሏል።

2.4. ገነተ ማርያም መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በማንዱራ ወረዳ የሚገኝ ሲሆን በውስጡም 2550 ሴት፣ 2476 ወንድ በድምሩ 5026 ተፈናቃዮች ይገኛሉ። በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች በ 2013ዓ.ም ከ ማንዱራ ወረዳ የተለያዩ ቀበሌዎች በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ሲሆን መንግስት ባዘጋጀው መጠለያ ጣቢያ ውስጥ እየተመዘገቡ መግባታቸውን እና ወደመጠለያ በሚገቡበት ወቅት እንዳይገቡ ምንም አይነት ክልከላ እንዳልተደረገባቸው ለማወቅ ተችሏል። በመጠለያ ጣቢያው የተፈናቃይ የመኖሪያ ክፍሎች በጣም የተጨናነቀ መሆኑን፣ የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ ወደመጠለያ ጣቢያው እንደገቡ በ 2 እና በ3 ወር ልዩነት ድጋፍ ይደረግላቸው የነበረ መሆኑን እና ከ2 አመት ወዲህ ምንም አይነት እርዳታ እያገኙ አለመሆኑን እና ፍራሽ፣ ብርድ ልብስ፣አንሶላ፣ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ እና የህጻናት አልሚ ምግብ ወደመጠለያው እንደገቡ ከ አራት አመት በፊት የተሰጣቸው መሆኑን እንዲሁም የህክምና አገልግሎት የሌለ በመሆኑ ችግር ውስጥ መሆናቸውን ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ለማወቅ ችሏል። በሌላ በኩል በግብረሰናይ ድርጅት አማካኝነት ህጻናት እስከ 2ኛ ክፍል ድረስ እንደሚማሩና 3ኛ ክፍል ሲገቡ በመደበኛው የመንግስት ትምህርት ቤት እንደሚማሩና የመማሪያ ቁሳቁስ አቅርቦት መኖሩን፣ በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ የጸጥታውን ሁኔታ የሚቆጣጠር አካል መኖሩን እንዲሁም ዘላቂ መፍትሄን በተመለከተ የነበሩበት አካባቢ ሰላሙ ተጠብቆላቸውና የሚቋቋሙበት ሁኔታ ተመቻችቶ ወደነበሩበት ቦታ ተመልሰው መኖር ፍላጎት እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል።

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የመተከል ዞን ግብርናና ገጠር ልማት መምሪያ ከተለያዩ አካባቢዎች ወደቀያቸውና ወደ ማዕከላት የተመለሱትን ተፈናቃዮች አስመልክቶ በደብዳቤ ቁጥር1386/5/ል/ጉ/7 በቀን 15/4/2017ዓ.ም ለኢሰመጉ በሰጡት ማስረጃ መሰረት እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል።

እስከ 1/4/2017ዓ.ም ድረስ ከከተማ ወደ ቀያቸው የተመለሱ የማህበረሰብ ክፍሎች

ተ.ቁ	ወረዳ	የቤተሰብ ኃላፊዎች			የቤተሰብ ብዛት		
		አባወራ	እማወራ	ድምር	ወንድ	ሴት	ድምር
1	ዳንጉር	3668	2035	5703	12493	12474	24967
2	ማንዱራ	701	390	1091	2476	2550	5026
3	ግልገል በለስ	359	331	690	1730	1781	3511

ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ለተፈናቃዮች የጊዜያዊ እርዳታ አቅርቦትን እና ዘላቂን መፍትሔ በተመለከተ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል ዞን ዋና አስተዳዳሪ እና ምክትል አስተዳዳሪ ጋር ውይይት ተደርጎ የነበረ ሲሆን ከጉብኝቱ በኋላም ኢሰመጉ ባደረገው ክትትል በግልገል በለስ 02 ቀበሌ ለነበሩት 392 አባወራ እና እማወራ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የተሰጣቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ተፈናቃዮችን ለማቋቋም ያደረገውን ጥረት በማጠናከር ሌሎች መጠለያ ጣቢያ ውስጥ ያሉ ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሄ የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዲያመቻች ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

3. ኦሮምያ ክልል

ኢሰመጉ በኦሮምያ ክልል በምስራቅ ሀረርጌ ዞን በጡሎ ፣ ደደር፣ ቦርደዴ፣ ሚኤሶ ፣ቲሬጉዶ፣ሙያደን፣ባቢሌ መጠለያ ጣቢያዎች እና ጅማ ከተማ እንዲሁም በምስራቅ ወለጋ ዞን ጎቡ ሰዮ ወረዳ አሞ እና በዲጋ ወረዳ አርጆ ጉደቱ መጠለያ ጣቢያዎች ከ 13/4/2017ዓ.ም - 11/11/2017ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ውስጥ ጉብኝት ያደረገ ሲሆን ግኝቶቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

3.1. የደደር መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በምስራቅ ሀረርጌ ዞን ደደር ወረዳ የሚገኝ ሲሆን በውስጡ 2795 ሴት ፣2195 ወንድ እና 1764 ህጻናት በድምሩ 6754 የሚገኙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 53 ወንድ፣ 36 ሴት እና 17 ህጻናት በድምሩ 106 የአካል ጉዳተኞች ይገኛሉ፡፡ በዚህ መጠለያ የሚገኙ ተፈናቃዮች በ2010ዓ.ም በግጭት ምክንያት ከሶማሌ ክልል ጅጅጋ የተፈናቀሉና በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ 7 አመታትን ያስቆጠሩ ሲሆን መጠለያ ጣቢያው በጣም የተጠጋጋና ጠባብ እና የተጨናነቀ እንዲሁም አካባቢው የንጽህና ጉድለት ያለበት በመሆኑ ለተላላፊ በሽታ እና ለእሳት አደጋ ሊያጋልጣቸው እንደሚችል ለመረዳት ተችሏል፡፡ ትምህርትን በተመለከተ በአካባቢው ባለ የመንግስት ትምህርት ቤት የሚማሩ ሲሆን የምግብ አቅርቦት የነበረ ቢሆንም ኢሰመጉ ጉብኝት ባደረገበት ወቅት በአመት አንዴ በሚያስብል ሁኔታ እየቀረበ መሆኑን፣ ለጨቅላ ህጻናት የሚሆን የተለየ የምግብ እና የቁሳቁስ አቅርቦት አለመኖሩን ፣በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ የህክምና አገልግሎት የሌለ ሲሆን መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት በተደረገ የመድሀኒት አቅርቦት ምክንያት መታከም የቻሉ ቢሆንም ከዛ ውጪ በግላቸው እንጂ ህክምና አቅርቦት አለመኖሩን፣ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ አቅርቦት መኖሩን፣የፍራሽ፣ብርድልብስና አንሶላ አቅርቦት አለመኖሩን እና ኢሰመጉ ጉብኝት ባደረገበት ወቅት በመጠለያ ጣቢያው በቋሚነትም ሆነ በግዜያዊነት እርዳታ የሚያቀርቡ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ባለመኖራቸው ድጋፍ እያገኙ አለመሆናቸውን ኢሰመጉ ለማወቅ ችሏል፡፡ በተጨማሪም የፍትህ ተቋማት ለተፈናቃይ ተደራሽ በሆነ መልኩ የሚገኝ ሲሆን በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ የጸጥታና የሰላም ሁኔታን የሚቆጣጠር አካል ያለ እና አለ መግባባቶች ሲፈጠሩ በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ በሚገኙ ኮሚቴዎች የሚፈታ መሆኑን እና መጠለያ ጣቢያው ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

አንድ ግለሰብ ስላሉበት ሁኔታ ሲያስረዱ«**በአንድ ክፍል ውስጥ ሁለት አባወራ ነው የምንኖረው እና እሱ በጣም ምቾት ይነሳል**›› «**እኔ የ1 አመት ጨቅላ ህጻን አለችኝ በምግብ እጥረት ምክንያት ተፈጥሮውን የጠበቀ እድገት የላትም መቀንጨር ገጥሟታል**»

«አሁን ያለንበት ቦታ ለመልሶ መቋቋም የማይመች ቦታ ነው ከዚህ አካባቢ ይልቅ የንግድ እንቅስቃሴ ያለበት ስለሆነ ወደ ባቢሌ ቢያዘዋውሩን በቀን ስራም ሆነ በሌላ መንገድ የምንጠቀምበት ሰፊ እድሎች አሉት» በማለት ገልጸዋል፡፡

3.2. ቦርደዴ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በምዕራብ ሀረርጌ ዞን ቦርደዴ ወረዳ የሚገኝ ሲሆን በውስጡም 797 ሴት እና 621 ወንድ በድምሩ 1418 ተፈናቃዮች ይገኛሉ፡፡ በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች በ2012 ዓ.ም በግጭት ምክንያት ከሶማሌ ክልል የተፈናቀሉ የኦሮሞ ተወላጆች ሲሆኑ ከቀያቸው በመፈናቀል ወደዚህ አካባቢ መምጣታቸውንና መንግስት እየመዘገበ ወደ መጠለያ ጣቢያው እንዳስገባቸው እንዲሁም ወደ መጠለያ ጣቢያው በገቡበት ወቅት አስፈላጊ የሆነውን ነገር ማለትም መጠለያ፣ ምግብ፣ የመጠጥ ፣ ውሃ እና የህክምና አገልግሎት ማግኘታቸውን እንዲሁም በመጠለያ ጣቢያውም ሆነ ከመጠለያ ጣቢያው ውጪ በነጻነት መንቀሳቀስ የሚችሉ ቢሆንም መታወቂያና ሌሎች ሊያስፈልጉ የሚችሉ ዶክመንቶች የተሰጣቸው አለመሆኑን፣ ትምህርትን በተመለከተ መጠለያ ጣቢያው ከከተማ የራቀ በመሆኑ በግብረ ሰናይ ድርጅት እርዳታ የተሰራ ከ 1-5ኛ ክፍል ለማስተማር የተዘጋጀ ትምህርት ቤት ያለ ሲሆን ከ5ኛ ክፍል በላይ የሆኑ ተማሪዎች ከተማ በመሄድ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ቢሆኑም በቁሳቁስ እጥረት ምክንያት ሁሉም መማር አለመቻላቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ በመንግስት የሚደረገው ድጋፍ በመጣ ጊዜ በአንድ ሰው 15 ኪሎ ግራም የሚሰጥ ሲሆን አንድ ግብረ ሰናይ ድርጅት በቋሚነት በእርሻ ስራ ላይ የሚያግዝ መሆኑን፣ ህክምናን በተመለከተ ጤና ጣቢያው ለመጠለያው ቅርብ ስለሆነ በጤና ጣቢያ የህክምና አገልግሎት እንደሚያገኙ፣ መጠለያ ጣቢያው የፍራሽ፣ አንሶላ፣ ብርድልብስ እና የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ እንዲሁም የህጻናት አልሚ ምግብ አቅርቦት አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡ የፍትህ ተቋማት ለተፈናቃይ ተደራሽ በሆነ መልኩ የሚገኙ ሲሆን በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ የጸጥታና የሰላም ሁኔታን የሚቆጣጠር አካል ያለ እና አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ በሚገኙ ኮሚቴዎች እና በአባገዳ የሚፈታ መሆኑን እና መጠለያ ጣቢያው ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ዘላቂ መፍትሄን በተመለከተ አንድ ግለሰብ «እኛ አሁን የምንፈልገው ከተረጅነት ተላቀን የራሳችን መኖሪያ መንግስት ሰቶን ወደስራየምንገባበት አደረጃጀት ነው» በማለት ገልጸዋል፡፡ ተፍናቃዮች ዘላቂ መፍትሄ እንዲሰጣቸው ቢፈልጉም መንግስት ግን ወደ መጡበት ለመመለስ፣ ካሉበት ማህበረሰብ ጋር ለመቀላቀልም ሆነ በዘላቂነት ወደሌላ ቦታ ለማስፈር የሚያደረገው እንቅስቃሴ ውስን እንደሆነ እና በተፈናቃይ ጣቢያው ረጅም ጊዜ የሆናቸው በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የስነልቦና ጫና ውስጥ ያሉ መሆኑን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡

3.3. ጡሎ/ሂርና መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በምዕራብ ሀረርጌ ጡሎ ወረዳ የሚገኝ ሲሆን በውስጡ 162 ሴት፣ 127 ወንድ እና 289 ህጻናት በድምሩ 578 ተፈናቃዮች የሚገኙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 3 ወንድ እና 2 ህጻናት በድምሩ 5 የአካል ጉዳተኞች ይገኛሉ፡፡ በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች በግጭት ምክንያት በ 2010 ዓ.ም ከሶማሌ ክልል የተፈናቀሉ ሲሆን በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ

ለ7 አመት ያህል ቆይተዋል፡፡ የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ ለ አንድ ሰው በነፍስ ወከፍ 15 ኪሎ ቦቆሎ የሚሰጥ ቢሆንም በ7 ወር እና በ8 ወር የሚሰጣቸው መሆኑን እና ተፈናቃዮች ወደ መጠለያ ጣቢያው ከገቡ በኋላ የተወለዱ ልጆች ያላቸው ቢሆንም የቤተሰብ ብዛት ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ ባለመሆኑ እና ለጨቅላ ህጻናት የሚሆን የተለየ ምግብ እና ቁሳቁስ ከ3 አመት በፊት የተሰጣቸው በመሆኑ ችግር ውስጥ መሆናቸውን፣ መጠለያ ጣቢያው ለተፈናቃዮች የፍራሽ፣ ብርድ ልብስ እና አንሶላ አቅርቦት የነበረው ቢሆንም ከተሰጣቸው እረጅም ጊዜ በመሆኑ ማለቁንና አዲስ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን እንዲሁም የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችም ከተሰጡ 3 አመት መሆኑን፣ ህክምናን በተመለከተ በመጠለያ ግቢ ውስጥ አነስተኛ ክሊኒክ እና ፋርማሲ ያለ መሆኑን እና ከክሊኒኩ አቅም በላይ ከሆነ በሪፈር ኡዳ ጤና ጣቢያ በመሄድ ህክምና እንደሚያገኙ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ትምህርትን በተመለከተ ልጆች ምንም አይነት መድሎና ጫና ሳይደረግባቸው ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው እንደሚማሩና ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ኮሌጆች በሚደርሱበት ጊዜ የአደጋ መከላከል ቢሮ የድጋፍ ደብዳቤን በመጻፍ ድጋፍ እንዲያገኙ እንደሚያደረግ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ልዩ ትኩረት ለሚያስፈልጋቸው ማለትም ለህጻናት የአልሚ ምግብ ይሰጥ የነበረ ቢሆንም አሁን ግን መቋረጡን እና ለነፍሰጡር እናቶች የእርግዝና ምርመራ እና ክትትል እንዲሁም ነጻ የመድኃኒት አቅርቦት መኖሩ፣ የፍትህ ተቋማት ለተፈናቃይ ተደራሽ በሆነ መልኩ የሚገኝ ሲሆን በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ የጸጥታና የሰላም ሁኔታን የሚቆጣጠር አካል ያለ እና አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ በሚገኙ ኮሚቴዎች የሚፈታ መሆኑን እና መጠለያ ጣቢያው ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ዘላቂነት ለማቋቋም ሆነ ወደመጡበት ለመመለስ የሚደረገው ጥረት አነስተኛ እንደሆነ ተፈናቃዮችም በከፍተኛ ችግር ውስጥ ያሉ መሆኑን በአካል በመገኘት ካደረግነው ምልከታ እና ኢሰመጉ ካሰባሰብ መረጃ ለመረዳት ችሏል፡፡ ተፈናቃዮች ወደመጠለያ ጣቢያው እንዳይገቡ የተደረገበት ሁኔታ ባይኖርም በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ሲያስረዱ፤ **‹‹መጠለያ ጣቢያው ፖሊስ ካምፕ አጠገብ ስለነበር/ የልዩ ሀይል/ካምፕ እና በማናውቀው ጉዳይ እናንተ ናችሁ የምትረብሹት እናንተ ከመጣችሁ በኋላ ነው እዚህ አካባቢ ረብሻ መከሰት የጀመረው በሚል ከዚህ ቀደም ከተፈናቃዮች ተመርጠው በውሃ ውስጥ እየተነከሩ የተደበደቡና የተገረፉ እንደነበሩ፤ ሆኖም ከዛ በኋላ በጥሩ ደህንነት ላይ እንዳሉ››** ገልፀዋል።

3.4. ጅማ መጠለያ ጣቢያ

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጅማ ዞን በሦስት ወረዳዎች ውስጥ ተፈናቃዮች የሚገኙ ሲሆን በጅማ ከተማ አስተዳደር ቡሳ ጎንፋ ቅርንጫፍ በተገኘ መረጃ መሰረት በጊንጆ ጉዱሪ/ ዲዲሲ/ እና ሰኮሩ ኢንዱስት መጠለያ ጣቢያ 615 ሴት፣ 1,767 ወንድ እና 1,135 ህጻናት በድምሩ 3,517 ተፈናቃዮች ይገኛሉ፡፡ በእነዚህ መጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙ ተፈናቃዮች ከምስራቅ

ሀረርጌ ዞን በደኖ ባለሸክ ቀበሌ በ2010 ዓ.ም በመሬት መንሸራተት ምክንያት የተፈናቀሉ ሲሆን በመጠለያ ጣቢያዎቹ ከሁለት ዓመት በፊት አልፎ አልፎ የተለያዩ አካላት ሰብዓዊ እርዳታ ያቀርቡ የነበረ ቢሆንም ከሁለት ዓመት ወዲህ ግን ምንም ዓይነት እርዳታ እያገኙ አለመሆኑን፣ የእለት ጉርሳቸውን የሚሸፍኑትም በከተማው ውስጥ ተንቀሳቅሰው በሚሰሩት የቀን ስራ ሲሆን የቀን ስራውን ማግኘት በማይችሉበት ጊዜ የእለት ጉርሳቸውን እንኳን መሸፈን የማይችሉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ትምህርትን በተመለከተ በመጠለያ ጣቢያ ውስጥ የመዋለ ህፃናት እና አንደኛ ክፍል ትምህርት የሚሰጥ ቢሆንም ከሁለተኛ ክፍል በላይ ለሆኑት በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ ትምህርት ቤት የሌለ በመሆኑ የማስተማር አቅም ያለው ሰው ብቻ ልጆቹን በአካባቢው በሚገኝ መደበኛ ት/ቤት አስገብቶ ያስተምራል።

የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ እና ለህፃናት ለአካል ጉዳተኛ ተብሎ የሚደረግ ድጋፍ አለመኖሩን እና መጠለያ ጣቢያው ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አለመሆኑን፣ የመጠልያ ጣቢያው ለተፈናቃዮች በቂ አለመሆኑንና የተጨናነቀ መሆኑን፣ በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ ለረጅም አመታት የቆዩ መሆኑንና ለመኖር ከባድ መሆኑን እንዲሁም ተፈናቃዮቹ መንግስትና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት መቋቋሚያ ቢሰጧቸው ወደለመዱት የግብርና ስራ ተመልሰው መደበኛ ኑሯቸውን መኖር እንደሚፈልጉ ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል።

በሌላ በኩል በመጠለያ ካሉት ተፈናቃዮች በተጨማሪ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩ ተፈናቃዮች መኖራቸውን የዞን አስተዳደሩ ቡሳ ጎኖፋ ቢሮ ለኢሰመጉ በሰጠው መረጃ ለማወቅ ተችሏል። እነዚህም በሁለት የተለያዩ ወረዳዎች የሚገኙ ሲሆን በጉማ ወረዳ በሊሙ ሻይ ከተማ የሚገኙ ተፈናቃዮች ብዛት 30 አባወራ፣ 135 የቤተሰብ አባላት በድምሩ 165 ተፈናቃዮች ቤት ተከራይተው የሚኖሩ ሲሆን 42 አባወራዎች፣ 317 የቤተሰብ አባላት በአጠቃላይ 359 ተፈናቃዮች ደግሞ በዘመድ አዝማድ ተጠግተው የሚኖሩ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል። በተመሳሳይ በጌራ ወረዳ ጪራ ከተማ የሚገኙ ተፈናቃዮች ብዛት 799 አባወራ፣ 2,930 የቤተሰብ አባላት በድምሩ 3,729 ተፈናቃዮች እንደሚገኙ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን እዚህ ወረዳ ላይ ተፈናቃዮችን ለማቋቋም የቤት መስሪያ መሬት በመለየት ላይ ሲሆን የቤት መስሪያ እንጨትም በከፊል ምላሽ መገኘቱን ቢሮው ለማረጋገጥ ችሏል። በተጨማሪም ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያው ከገቡ እረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደመጡበት ለመመለስ ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን ኢሰመጉ ለማወቅ ችሏል።

3.5. ቲሬጉዶ /ጭናቅሰን መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በምስራቅ ሀረርጌ ዞን ጭናቅሰን ወረዳ የሚገኝ ሲሆን 235 ሴት እና 2,66 ወንድ በድምሩ 500 ተፈናቃዮች ይገኛሉ። እነዚህ ተፈናቃዮች ከሶማሌ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በ 2010 ዓ.ም የተፈናቀሉ ሲሆን ወደመጡበት አካባቢ እንዲመለሱ ማድረግ የተቻለ ቢሆንም

ድጋሚ በተነሳ ግጭት ምክንያት በድጋሚ ሊፈናቀሉ ችለዋል ። ተፈናቃዮች የሚገኙበት መጠለያ ጣቢያ በሶማሌ እና ኦሮምያ ድንበር አካባቢ የሚገኝ በመሆኑ እና ለዳግም ጥቃት ተጋላጭ የሚያደርጋቸው በመሆኑ ተፈናቃዮች ወደሌላ አካባቢ መጠለያ ጣቢያው እንዲዛወርላቸው ጠይቀው የነበረ ቢሆንም ምላሽ ባለማግኘታቸው ከፍተኛ ስጋት ውስጥ መሆናቸውን ለኢሰመጉ ገልጸዋል። በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ በተፈናቃዮች የተሰራ 100 የዳስ ቤቶች የሚገኙ ሲሆን የመጠለያ ቤቶቹ በጣም ጠባብ እና የተጨናነቀ መሆን፣ ጣሪያው ለዝናብ የተጋለጠ መሆን እና መጠለያ ጣቢያው ያለበት አካባቢ ለደህንነት ስጋት የተጋለጠ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡ ፡ የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ ጥራቱን የጠበቀ አለመሆን እና መስከረም ወር 2017ዓ.ም የቀረበላቸው ቢሆንም ከዛ በኋላ ቀርቦላቸው የሚያውቅ አለመሆኑን፣ የህፃናት አልሚ ምግብ አቅርቦት የነበረ ቢሆንም ከተወሰኑ ጊዜያት በፊት መቋረጡን፣ ትምህርት ቤቶች ከመጠለያ ጣቢያው እሩቅ በመሆናቸው ህጻናት የትምህርት አገልግሎት እያገኙ አለመሆኑን እና የጤና መድን ክፍያ መክፈል ባለመቻላቸው የህክምና አገልግሎት ማግኘት አለመቻላቸውን እንዲሁም የፍራሽ፣ብርድልብስ እና አንሶላ አቅርቦት ወደመጠለያ ጣቢያው በገቡ ወቅት የተሰጣቸው እና እረጅም ጊዜ የሆነው በመሆኑ ማለቁን ፣ ተፈናቃዮች መሆናቸውን የሚገልጽ መታወቂያ ያላቸው መሆኑን እና በአካባቢው ተንቀሳቅሰው መስራት የሚችሉ መሆኑን እንዲሁም አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በመጠለያ ጣቢያው በተዋቀሩ የሰላም ኮሚቴዎች እንደሚፈታ እና በአቅራቢያቸውም የጸጥታና የፍትህ አካላት መኖራቸውን ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ለማወቅ ችሏል። በተጨማሪም ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያው ከገቡ እረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደመጡበት ለመመለስ ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን ኢሰመጉ ለማወቅ ችሏል።

3.6. ሙያዲን ካምፕ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በምስራቅ ሀረርጌ ዞን በጉርሱም ወረዳ የሚገኝ ሲሆን 654 ሴት እና 280 ወንድ በድምሩ 934 ተፈናቃዮች የሚገኙ ሲሆን እነዚህ ተፈናቃዮች ከሶማሌ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በ 2010 ዓ.ም የተፈናቀሉ ናቸው። መጠለያ ጣቢያው የወታደር ካምፕ የነበረ እና 8 መጋዘን ቤቶች ያሉት ሲሆን ቤቶቹ ከተፈናቃይ ብዛት ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆናቸው ተፈናቃዮቹ በተጨናነቀ ሁኔታ ውስጥ እየኖሩ መሆኑን፣ የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ ከተቋረጠ 7ወር መሆኑን ፣ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ኢሰመጉ ጉብኝት ባደረገበት ወቅት ተቋርጦ የነበረ መሆኑን፣ የህፃናት አልሚ ምግብ ባለመኖሩ ለልመና እና ለጎዳና መዳረጋቸው፣ ትምህርት ቤቱ ከመጠለያ ጣቢያው እሩቅ በመሆኑ ህፃናት የትምህርት አገልግሎት እያገኙ አለመሆናቸውን፣ የህክምና አገልግሎት ለማግኘት እንደማንኛውም የአካባቢው ማህበረሰብ የጤና መድን ክፍያ መክፈል ስላለባቸው መክፈል ባለመቻላቸው ምክንያት አገልግሎት እያገኙ አለመሆናቸውን እና የፍራሽ፣ብርድልብስ እና አንሶላ አቅርቦት ወደመጠለያ ጣቢያው በገቡ ወቅት የተሰጣቸው እና እረጅም ጊዜ የሆነው በመሆኑ ማለቁን እንዲሁም ተፈናቃዮች መሆናቸውን የሚገልጽ መታወቂያ

ያላቸው መሆኑን፣ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በመጠለያ ጣቢያው በተዋቀሩ የሰላም ኮሚቴዎች እንደሚፈታ እና በአቅራቢያቸውም የጸጥታና የፍትህ አካላት መኖራቸውን ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ለማወቅ ችሏል።

በተጨማሪም የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ አቅርቦት አለመኖሩን እና ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያው ከገቡ እረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደመጡበት ለመመለስ ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን ኢሰመጉ ለማወቅ ችሏል።

3.7. ባቢሌ መጠለያ ጣቢያ

በዚህ አካባቢ መጠለያ ጣቢያ በምስራቅ ሀረርጌ ዞን በባቢሌ ወረዳ ባቢሌ ት/ቤት የሚገኝ ሲሆን 326 ሴቶች እና 313 ወንዶች በአጠቃላይ 639 የሚገኙ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 407 ህጻናት ናቸው። በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች በ2010ዓ.ም ከሶማሌ ክልል በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ሲሆን በዚህ መጠለያ ጣቢያ ይኖሩ የነበሩ ተፈናቃዮች ኢሰመጉ ጉብኝት ባደረገበት ወቅት በቅርብ ዘመድ አዝማዳቸው ጋር ተጠግተው እየኖሩ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል። በዚህ አካባቢ የሚገኙት ተፈናቃዮች ከፍተኛ የሆነ የመጠለያ ቤት ችግር ያለባቸው መሆኑ በአሁኑ ጊዜም ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው ቤት መከራየት የቻለ ተከራይቶ ያልቻለ ከሰው ቤት ተጠግቶ እንደሚኖር፣ የምግብ አቅርቦቱ ወቅቱን ጠብቆ እንደማይቀርብ እና ጥራቱን የጠበቀ አለመሆኑን፣ በወቅቱ በጥራት መጠኑን ጠብቆ ያለመቅረብ አልፎ ቀሉብ ከተሰጣቸው ከሁለት ዓመት በላይ መሆኑን፣ የህፃናት አልሚ ምግብ አለመኖሩን እና ህጻናት ትምህርት እያገኙ አለመሆኑን እንዲሁም የህክምና አገልግሎት የጤና መድን ክፍያ መክፈል ባለመቻላቸው ምክንያት አገልግሎት ማግኘት አለመቻላቸውን ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ለማወቅ ችሏል።

በተጨማሪም መንግስት በዘላቂነት ለማቋቋም የሚያደርገው ጥረት አንስተኛ መሆኑን እና ተፈናቃዮች ለከፍተኛ ችግር የተዳረጉ መሆኑን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል።

3.8. አኖ ከተማ 01 ቀበሌ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በምስራቅ ወሊጋ ዞን ጎቡ ሰዮ ወረዳ አኖ ከተማ 01ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን 2,342 ሴት፣844 ወንድ እና 1,524 ህጻናት በአጠቃላይ 4,710 ተፈናቃዮች ይገኛሉ። በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ አካል ጉዳተኞች ያሉ ቢሆንም ብዛታቸውን የያዘ ዳታ ባለመኖሩ ቁጥራቸውን ማወቅ አልተቻለም። አብዛኛዎቹ ተፈናቃዮቹ ከሚኖሩበት ጎቡ ሰዮ ወረዳ እና ከአጎራባች ከሆነው ስቡ ስሬ ወረዳ ከአራት ዓመት ፊት በ2014 ዓ.ም በአካባቢያቸው በነበር ግጭት የተነሳ የተፈናቀሉ ሲሆን የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ በነፍስ ወከፍ በወር 15 ኪሎ የበቆሎ ዱቄት የሚቀርብ

ቢሆንም አብስለው ለመመገብ የሚያስችላቸውን ዘይት፣ ጨው፣ ሽንኩርት፣ እንጨት ለመግዛት ከተሰጣቸው ዱቄት ላይ ቀንሰው ለመሸጥ እንደሚገደዱ እና በዚህም ምክንያት የሚሰጣቸው ዱቄት ለወር የማይበቃ በመሆኑ ችግር ውስጥ መውደቃቸውን፣ የህክምና አገልግሎት ባለመኖሩ ለነፍሰጡር እናቶች የሚደረግ የጤና ክትትል አለመኖሩን፣ የህጻናት ትምህርትን በተመለከተ በመጠለያ ጣቢያው ለም ይህም በመሆኑ አቅም ያለው ልጆቹን በመደበኛ ትምህርት ቤት የሚያስተምር ሲሆን አብዛኛው ወላጅ ለደብተር እስኪርብቶና ዩኒፎርም መግዣ የሌለው በመሆኑ ህፃናት ከትምህርት ገበታ ውጪ መሆናቸውን፣ፍራሽ ፣ብርድ ልብስ፣አንሶላ እንደገቡ የተሰጣቸው ሲሆን ያረጀመሆኑን፣ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ አቅርቦት አለመኖሩን እና መጠለያ ጣቢያው ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል። መጠለያ ጣቢያው የሚገኘው በትንሽ ከተማ ውስጥ በመሆኑ ተፈናቃዮች በግላቸው ተንቀሳቅሰው ለመስራት የሚያስችል የስራ እድል አለመኖሩን እና ከአካባቢው የጸጥታ ችግር አንጻር ከከተማ ውጪ መንቀሳቀስ አለመቻላቸውንና ይህም በመሆኑም ከፍተኛ የሆነ የደህንነት ስጋት መኖሩንበ ተጨማሪም ተፈናቃዮች ከተፈናቀሉ እረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደመጡበት ለመመለስ ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ካሰባሰበው መረጃ ለማወቅ ችሏል።

3.9. አርጆ ጉደቱ ከተማ 01 ቀበሌ መጠለያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በምስራቅ ወለጋ ዞን ዲጋ ወረዳ ጉዳቱ አርጆ ከተማ 01 የሚገኝ ሲሆን 1,123 ሴት፣ 1,047 ወንድ እና 1,756 ህጻናት በአጠቃላይ 3,926 ተፈናቃዮች ይገኛሉ። እነዚህ ተፈናቃዮች በአካባቢያቸው በነበረው ግጭት የተነሳ በ2014 ዓ.ም የተፈናቀሉ ናቸው። የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ በነፍስ ወከፍ 7 ኪ.ግ በቆሎ በአማካይ ከ3 እስከ 4 ወር ጊዜ ውስጥ የሚሰጥ ይህም በቂ ባለመሆኑ መቸገራቸውን፣ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሴቶች፣ ህጻናትና አካል ጉዳተኞች የተለየ ድጋፍ አለመኖሩን፣ የህክምና አገልግሎት ባለመኖሩ ለነፍሰጡር እናቶች የሚደረግ የጤና ክትትል አለመኖሩን ፣ መጠለያ ጣቢያው ጠባብ በመሆኑና የሚጠቀሙትም የቀበሌ ፅ/ቤቱን ግማሽ እንዲሁም የተወሰኑ ድንኳን ጥለው ሲሆን ይህም ቢሆን በአካባቢው ከሚገኘው ተፈናቃያ ቁጥር ጋር ሊመጣጠን ባለመቻሉ የተወሰኑት በግላቸው ተከራይተው እና ከመህበረሰብ ተጠግተው እንደሚኖሩ ለማወቅ ችለናል። የፍራሽ፣ብርድ ልብስ አቅርቦት እንደሌለ፣ የሴቶች ንፅህና መጠበቂያ አቅርቦት እንደሌለና አቅም ያላቸውና በዘመድ አዝማድ የሚደጎሙ ጥቂት ተፈናቃዮች ልጆቻቸውን መደበኛ ትምህርት ለማስተማር የቻሉ ሲሆን አብዛኛው ተፈናቃይ ከራሳቸው አልፈው ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት ለመላክ አቅም የሌላቸው በመሆኑ ህጻናት ትምህርት እያገኙ አለመሆኑን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለማወቅ ችሏል። ተጨማሪም ተፈናቃዮች ከተፈናቀሉ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደመጡበት ለመመለስ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ካሰባሰበው መረጃ ለማወቅ ችሏል።

3.10. ገንደ ለሚ የተፈናቃዮች ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በምዕራብ ሀረርጌ ዞን ጉንቢ ቦርደዴ ወረዳ በ 01 ቀበሌ ገንደ ለሚ የሚገኝ ሲሆን በውስጡ 797 ሴት፣ 621 ወንድ እና 5 አካል ጉዳተኛ በአጠቃላይ 1,423 ተፈናቃዮች ይገኛሉ። መጠለያ ጣቢያው ከቆርቆሮ እና ከጨፈቃ ምርጊት የተሰሩ 180 ብሎኮችና 604 ክፍሎች ያሉት ሲሆን በአማካይ 4 በ 7 ሜትር ስፋት ያላቸው ሳሎን እና መኝታ ክፍሎች ውስጥ ከ 5 - 9 ሰዉ ይኖርባቸዋል። በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙት ተፈናቃዮች በመስከረም ወር 2010 ዓ.ም ከሶማሌ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ሲሆን መጀመሪያ እንደተፈናቀሉ መሰላ ወረዳ አካባቢ ለተወሰኑ ጊዜያት ከቆዩ በኋላ ከቦርደዴ ከተማ በቅርብ ርቀት ላይ በምትገኘው 01 ቀበሌ ገንደ ለሚ ተብሎ ወደሚጠራዉ የተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያ የገቡ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ በነፍስ ወከፍ 15 ኪሎ ግራም ስንዴ ወይም በቆሎ የሚቀርብ ሲሆን ይህም በአማካኝ ከ 5 እስከ 7 ወር ቆይቶ እንደሚሰጣቸውና ጥራቱን የጠበቀ አለመሆኑን፣ የህጻናት አልሚ ምግብ አለመኖሩን፣ ከንጽህና መጠበቂያ ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ ቁሳቁሶች መኖራቸውን፣ ፍራሽ፣ አንሶላና ብርድ ልብስ ወደመጠለያ ጣቢያው በገቡ ወቅት አንድ ጊዜ ብቻ የተሰጣቸው መሆኑን፣ ህክምናን በተመለከተ በግብረሰናይ ድርጅት የተቋቋመ የጤና ማዕከል የነበረ ቢሆንም ስራ ካቆመ አንድ አመት በመሆኑ የጤና እክል ሲገጥማቸው በወረዳው በሚገኘው የጤና ጣቢያ አገልግሎት የሚያገኙ መሆኑን እና የጤና መድን ክፍያ በቦርደዴ ወረዳ እንደሚሸፈን ለማወቅ ተችሏል።

ትምህርትን በተመለከተ መጠለያ ጣቢያው ውስጥ የመዋዕለ ህጻናት እና የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ያለ ሲሆን ለመዋዕለ ህጻናት የተሰራው ትምህርት ቤት በቆርቆሮ የተሰራ በመሆኑ በአውሎ ንፋስ አደጋ የደረሰበት እና የፈራረሰ ቢሆንም ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የሚሰራ መሆኑን የወረዳው ሀላፊዎች ለኢሰመጉ ገልጸዋል። በተጨማሪም ለህጻናት ማቆያ የሚሆን ሙሉ ቁሳቁስ የተሟላለት ማዕከል መኖሩ እና ለተማሪዎች የሚሰጣቸዉ የትምህርት መማሪያ ቁሳቁስ ከመስከረም 2017 ዓ/ም ጀምሮ አቅርቦት መኖሩን ለማወቅ ችሏል።

በሌላ በኩል መጠለያ ጣቢያዉ የሚገኝበት ቦታ ምንም አይነት የፀጥታ ችግር አለመኖሩን እና መጠለያ ጣቢያውን የሚጠብቁ የተመደቡ ሰዎች በመኖራቸው ለደህንነት አስጊ አለመሆኑን፣ መጠለያ ጣቢያዉ የሚገኝበት ቦታ ለአካል ጉዳተኞችና ለህጻናት ምቹ አለመሆኑን፣ የመጠጥ ውሃ ዕጥረት እንዳይከሰት በአራት አቅጣጫ ባለ 20 ሺ ሊትር ውሀ የሚይዙ ሮቶዎች አገልግሎት የሚሰጡ መሆኑን እና በወረዳው በሚገኙ መስሪያ ቤቶች የስራ እድል እንዲያገኙ መደረጉን ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ለማወቅ ችሏል።

3.11. ገንደ ድንቁ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በምዕራብ ሀረርጌ ዞን በጡሎ ወረዳ 01 ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን ከሂርና ከተማ በቅርብ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ መጠለያ ጣቢያው በውስጡ 239 ሴት፣ 187 ወንድ እና 3 ወንድ አካል ጉዳተኞ በአጠቃላይ ከ 429 በላይ ተፈናቃዮች ይገኛሉ፡፡ መጠለያ ጣቢያው ከቆርቆሮ የተሰሩ 6 ብሎኮችና 85 ክፍሎች ያሉት ሲሆን በአማካይ 3 በ 4 ሜትር ስፋት ባላቸው መኝታ ክፍሎች ውስጥ ከ 5 - 9 ሰዉ ይኖርባቸዋል፡፡ ከመጠለያ ጣቢያው ውጪ በየሰው ቤት ጥገኝነት በከተማዋ እና በገጠር የሚኖሩ 52 አባወራዎች ያሉ ሲሆን እነዚህ ተፈናቃዮች ተፈናቅለው በመጡ ወቅት መጠለያ ጣቢያዎችን ለመስራት በቂ በጀት ባለመኖሩ ምክንያት ወደመጠለያ ሳይገቡ የቀሩ ሲሆኑ እና በየጊዜው እየተመላለሱ መጠለያ እንዲሰጣቸው የሚጠይቁ ቢሆንም ኢሰመጉ ጉብኝት እስካደረገበት ጊዜ ድረስ መጠለያ ያልተሰጣቸው መሆኑን እና በከፍተኛ ችግር ውስጥ እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙት ተፈናቃዮች በመስከረም ወር 2010 ዓ.ም ከሶማሌ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ናቸው፡፡

የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ በነፍስ ወከፍ 15 ኪሎ ስንዴ ወይም በቆሎ የሚቀርብ ሲሆን ይህም በአማካኝ ከ5 እስከ 8 ወር ቆይቶ እንደሚሰጣቸውና ጥራቱን የጠበቀ አለመሆኑን እና የህጻናት አልሚ ምግብ ባለመኖሩ የህጻናት አስተዳደግ እና የጤና ሁኔታ ችግር እየፈጠረ መሆኑን፣ከንጽህና መጠበቂያ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ቁሳቁሶች በቂ አለመሆናቸውን፣ ፍራሽ፣ አንሶላና ብርድ ልብስ ወደመጠለያ ጣቢያው በገቡ ወቅት አንድ ጊዜ ብቻ የተሰጣቸው ሲሆን ለመጠቀም በሚያስችል ሁኔታ ላይ የማይገኝ በመሆኑ በጣም መቸገራቸውን ለኢሰመጉ ገልጸዋል፡፡ ህክምናን በተመለከተ በግብረሰናይ ድርጅት የተቋቋመ የጤና ማዕከል የነበረ ቢሆንም ስራ ካቆመ አንድ አመት በመሆኑ የጤና እክል ሲገጥማቸው በጣም እየተቸገሩ መሆኑን፣ ትምህርትን በተመለከተ በቅርበት ት/ቤት ባለመኖሩ ምክንያት አቅም ያለዉ እና አመላለሶ ማስተማር የቻሉ ጥቂቶች ብቻ እያስተማሩ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል መጠለያ ጣቢያዉ የሚገኝበት ቦታ ምንም አይነት የፀጥታ ችግር የሌለበት እና መጠለያ ጣቢያውን የሚጠብቁ የተመደቡ ሰዎች ቢኖሩም ግቢው አጥር እና የመብራት አገልግሎት የሌለው በመሆኑ እና ዙሪያው ጫካ በመሆኑ አራዊቶች የሚወጡ በመሆኑ ለደህንነታቸው አስጊ መሆኑን፣መጠለያ ጣቢያዉ የሚገኝበት ቦታ ለአካል ጉዳተኞችና ለህጻናት ምቹ አለመሆኑን እና የመጠጥ ውሃ ዕጥረት መኖሩን ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ለማየት ችሏል፡፡

3.12. ሊጊደ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ሀረርጌ ዞን በጎሮ ጉቱ ወረዳ 01 ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን ከካራሚሌ ከተማ በቅርብ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ መጠለያ ጣቢያው በውስጡ 223 ሴት

፣ 237 ወንድ በአጠቃላይ 460 ተፈናቃዮች የሚገኙ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 167 ህጻናት እና 5 አካል ጉዳተኞች ይገኛሉ፡፡ መጠለያ ጣቢያው ከቆርቆሮ እና ከሸራ የተሰሩ 2 ብሎኮችና 78 ክፍሎች ያሉት ሲሆን በአማካይ 3 በ 3 ሜትር ስፋት ባላቸው የመኝታ ክፍሎች ውስጥ ከ 5 - 9 ተፈናቃዮች ይኖራሉ፡፡ በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙት ተፈናቃዮች በመስከረም ወር 2010 ዓ.ም ከሶማሌ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ናቸው፡፡ የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ በነፍስ ወከፍ 15 ኪሎ ስንዴ ወይም በቆሎ በአማካኝ ከ 7 እስከ 10 ወር ውስጥ ይቀርብ የነበረ ሲሆን ከመስከረም ወር 2017 ዓ.ም በኋላ አቅርቦት አለመኖሩን፣ በዚህም ምክንያት ህጻናት ላይ ከፍተኛ የሆነ የጤና ጉዳት እያስከተለ መሆኑን፣ ከንጽህና መጠበቂያ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ቁሳቁሶች በቂ አለመሆኑን ፣ ፍራሽ፣ አንሶላና ብርድ ልብስ ወደመጠለያ ጣቢያው በገቡ ወቅት አንድ ጊዜ ብቻ የተሰጣቸው መሆኑን እና በጣም መቸገራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ህክምናን በተመለከተ በግብረሰናይ ድርጅት የተቋቋመ የጤና ማዕከል የነበረ ቢሆንም ስራ ካቆመ አንድ አመት በላይ በመሆኑ የጤና እክል ሲገጥማቸው በጣም እየተቸገሩ መሆኑን፣ ትምህርትን በተመለከተ በቅርበት ት/ቤት ባለመኖሩ ምክንያት በወረዳው ባለው መደበኛ ትምህርት ቤት ልጆቻቸውን ልከው እያስተማሩ ቢሆንም በተማሪዎች እና በመምህራን አድሎ እንደሚደረግባቸው እና የመማር ሞራላቸው እየተሸረሸረ መሆኑን ለኢሰመጉ ገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩል መጠለያ ጣቢያዉ የሚገኝበት ቦታ ምንም አይነት የፀጥታ ችግር የሌለበት ቢሆንም መጠለያ ጣቢያዉ የሚገኝበት ቦታ ለአካል ጉዳተኞችና ለህጻናት ምቹ አለመሆኑን፣ በመጠለያ ጣቢያዉ የመጠጥ ዉሃ ዕጥረት እንዳለ ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ለማወቅ ችሏል፡፡

3.13. ቀርሳ ካምፕ (ቴክኒክና ሙያ) መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በ ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ቀርሳ ወረዳ በ 02 ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን በውስጡ 365ሴት፣ 299 ወንድ፣ 1584 ህጻናት እና 7 አካል ጉዳተኞች በአጠቃላይ 2,255 ተፈናቃዮች ይገኛሉ፡፡ በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙት ተፈናቃዮች ከመስከረም 2010 ዓ.ም ጀምሮ ከጅጅጋ፣ ከውጫሌ እና የተወሰኑት ከጅቡቲ በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ናቸው፡፡ 100 አባወራዎች በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ ሲገኙ አንዳንድ ተፈናቃዮች በዘመድ ቤት እንደሚኖሩና ስራ ፍለጋ ወደ ድሬዳዋ እንደሚሄዱ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ይህም የሆነው የምግብ አቅርቦት በመቋረጡና ቤተሰቦቻቸውን ለማኖር መስራት አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡ ህክምናን በተመለከተ በአለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅት የሚደረግላቸው ድጋፍ ቢኖርም የተሟላ አለመሆኑን፤ የህፃናት ትምህርትን በተመለከተ ህጻናት በመጠለያው ውስጥ የትምህርት አገልግሎት እያገኙ ሲሆን በመበኛ ትምህርት ቤት ገብተው የሚማሩ መኖራቸውን እና በወቅቱ የትምህርት ቁሳቁስ ማግኘቱ መቸገራቸውን ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለማወቅ ችሏል፡፡

3.14. 01 ቀበሌ የጎልማሳ ማህበረሰብ መጠለያ ጣቢያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ ምስራቅ ሀረርጌ ዞን በደደር ወረዳ 01 ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን በውስጡ 2,466 ሴት፣ 2,282 ወንድ በአጠቃላይ 4,748 ተፈናቃዮች ይገኛሉ። በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙት ተፈናቃዮች በመስከረም ወር 2010 ዓ.ም ከሶማሌ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ናቸው።

የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ በነፍስ ወከፍ 12 ኪ.ግ ማሽላ የሚሰጥ ሲሆን በቂ እና ጊዜውን ጠብቆ እንደማይቀርብ በዚህም ምክንያት አባወራዎችም እየተሰደዱ ወደ ሌላ አካባቢ በመሄድ ላይ መሆናቸውን እና ከመንግስት የተመደበ ምንም አይነት በጀት አለመኖሩን፣ ጤናን በተመለከተ አለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅት የ 3 ዓመት የጤና መድን ክፍያ የከፈለላቸው ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን ክፍያው እየጨመረ በመሄዱና ክፍያውም በመቋረጡ ለችግር መዳረጋቸውን፣ ህጻናት የትምህርት አገልግሎት የሚያገኙ ቢሆንም ትምህርት ቤቱ ከመጠለያ ጣቢያው እሩቅ በመሆኑ ለትራንስፖርት ወጪ መዳረጋቸውን እና የዩኒፎርምና የትምህርት ቁሳቁስ አቅርቦት ባለመኖሩ ትምህርታቸውን ለመከታተል ተግዳሮት መሆኑን እና ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ምክንያት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

መጠለያ ጣቢያው ውስጥ የፀጥታና ሰላም ሁኔታን የሚቆጣጠር ያለ ቢሆንም አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በቅርበት ባለው ቀበሌ የሚዳኙ መሆኑን፣ መጠለያ ጣቢያው ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አለመሆኑን፣ ተፈናቃዮች ወደመጠለያ ጣቢያው ከገቡ በኋላ የተወለዱ ልጆች በመኖራቸው እና የቤተሰብ አባላቶቻቸው እየበዙ በመምጣታቸው በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ መጨናነቅ መፍጠሩን፣የብርድ ልብስ፣ አንሶላና ፍራሽ አቅርቦት የነበረ ቢሆንም ከተቋረጠ ሁለት አመት መሆኑን እና ተፈናቃዮች ከተፈናቀሉበት አካባቢ እነሱን እየፈለጉ የሚመጡት ሰዎች በመኖራቸው ለአካባቢው ስጋት መሆናቸውን ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ከተፈናቃዮችና ከአደጋ ስጋት ባገኘው መረጃ ለማወቅ ችሏል።

3.15. የግራዋ ወረዳ 02 ቀበሌ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በምስራቅ ሀረርጌ ዞን በግራዋ ወረዳ ግራዋ ከተማ 02 ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን በውስጡ 93 ሴት፣ 120 ወንድ በአጠቃላይ 213 ተፈናቃዮች ይገኛሉ ከነዚህ ውስጥ 15 አካል ጉዳተኞች እና 3 ህፃናት ይገኙበታል። በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙት ተፈናቃዮች በመስከረም ወር 2010 ዓ.ም ከሶማሌ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ሲሆን መጠለያ ጣቢያው በከተማ ውስጥ የሚገኙ የተወረሱ የመንግስት ቤቶች ሲሆን ጣሪያው በመቀደዱ እና የሚያፈስ መሆኑን የላስቲክ ሽራ ቤት ውስጥ በመዘርጋት ለመከላከል እንደሚሞክሩ እና ከቆይታ ብዛት የቤቶቹ ግድግዳ ፈራርሶ ቀዳዳውን በጨርቅ በመሸፈን እየኖሩ

መሆኑን እና በዚህም ምክንያት ልጆቻቸው ለተለያዩ አደጋዎች ተጋላጭ በመሆናቸው ሌሊቱን በየተራ እየጠበቁ እንደሚያድሩ ለማወቅ ተችሏል።

የምግብ አቅርቦት ከተቋረጠ 2አመት ያለፈው በመሆኑ ከፍተኛ ችግር ውስጥ መሆናቸውን፣ የህጻናት ትምህርትን በተመለከተ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ቢሆንም ትምህርት ቤቱ ከመጠለያ ጣቢያው እጅቅ በመሆኑ ከ 2 ኪሎ ሜትር በላይ ይጓዛሉ፣ በተጨማሪም ዩኒፎርም እና የትምህርት ቁሳቁስ አቅርቦት ባለመኖሩ ለቀጣዩ የትምህርት ወቅቶች ልጆቻቸው ትምህርት ላይቀጥሉ የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩን ተፈናቃዮች ለኢሰመጉ ገልጸዋል።

በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ የጤና ተቋም የሌለ ሲሆን በመንግስት የጤና ተቋም የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል ወረቀት ከመጠለያ ጣቢያው የሚጻፍላቸው ቢሆንም የመድሀኒት አቅርቦት ማግኘቱ አስቸጋሪ መሆኑን፣ የጸጥታና ሰላም ሁኔታን የሚቆጣጠር ባይኖርም አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በአካባቢው በሚገኙ የፀጥታ አካላት የሚፈታ መሆኑን፣ የመጠለያ ጣቢያው ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አለመሆኑን ኢሰመጉ ለማወቅ ችሏል።

በመጠለያ ጣቢያዎቹ የሚገኙ ተፈናቃዮች ከአምስት አመት በላይ የሆናቸውና በአብዛኛው ትኩረት እየተሰጠ ያለው ገጠር ውስጥ ላሉት መጠለያ ጣቢያዎች በመሆኑ በተቻለ አቅም እነዚህን ወደሌላ አካባቢ ቋሚ ሆነው አርሰው ወደሚበሉበት (ወደሚኖሩበት) አካባቢ ማዛወር ወይም በከተማ ውስጥ ቋሚ በሆነ ስራ ማደራጀት ካልተቻለ ኑሮአቸው አስጊ በመሆኑ መፍትሄ ሊሰጣቸው እንደሚገባ የወረዳው የአደጋ ስጋት ለኢሰመጉ ገልጸዋል።

4. አማራ ክልል

በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች በተነሱ ግጭቶችና የሰላም እጦት ምክንያት በተለያዩ ጊዜያትና ከተለያዩ አካባቢዎች ተፈናቅለው በአማራ ክልል የሚገኙ ተፈናቃዮችን ማለትም ግብርና ጊቢ፣ መካነ ኢየሱስ፣ ላምእርባታ እና ከመጠለያ ውጪ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው ያሉ ተፈናቃዮችን ከ 13/4/2017ዓ.ም - 18/4/2017 ዓ.ም እና በማዕከላዊ ጎንደር ዞን ጎንደር ከተማ ቀበሮ ሜዳ እና በሰሜን ጎንደር ዞን ዳባት ወረዳ ሺመላኩ መጠለያ ጣቢያ ያሉ ተፈናቃዮችን ከመጋቢት 23- 27 / 2017 ዓ/ም እና ከግንቦት 30-8/2017 ዓ.ም፣ የወይንሸት፣ ቻይና ካምፕ፣ ገራዶ፣ ቻይና ካምፕ/ ደጋን፣ ገራዶ፣ መዲና፣ ኮሌጅ ጊቢ፣ አባሬ፣ ጃራ፣ መርሳ፣ሸዋሮቢት፣ አጣዬ፣ ኤፍራታና ግድም ወረዳ እና ምንጃርሸንኮራ የሚገኙ መጠለያ ጣቢያዎችን ኢሰመጉ ጉብኝት ያደረገ ሲሆን ግኝቶቹ እንደሚከተለው ቀርቧል::

4.1. መካነ ኢየሱስ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በሀይቅ ከተማ ተሁለደሬ ወረዳ የሚገኝ ሲሆን በውስጡም 726 ሴት፣ 688 ወንድ እና 647 ህጻናት በድምሩ 2,061 ተፈናቃዮችን የያዘ ሲሆን ከነዚህ ውስጥም 22 ወንድ፣ 10 ሴት በድምሩ 32 አካል ጉዳተኞችን ይዟል:: በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች በ2013 ዓ.ም ከ ኦሮምያ ክልል ከተለያዩ የወለጋ ዞኖች በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ሲሆኑ ወደ መጠለያ ጣቢያው እንደገቡ ፍራሽ፣ ብርድ ልብስና አንሶላ መጠለያ ጣቢያው ያቀረበላቸው ቢሆንም ከተሰጣቸው ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ በመሆኑ ፍራሽ፣ ብርድ ልብስና አንሶላው ማርጀቱንና ለመልበስ በሚያስችል ደረጃ ላይ አለመሆኑን፣ ለሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ እንዲሁም ለጨቅላ ህጻናት የሚሆን የአልሚ ምግብ እና የቁሳቁስ አቅርቦት አለመኖሩን መጠለያ ጣቢያው የተጨናነቀና ጠባብ መሆኑን ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ለማወቅ ችሏል:: ትምህርትን በተመለከተ የመደበኛ ትምህርት ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው የሚማሩ መሆኑን፣ ህክምና ያለ ቢሆንም የመድሀኒት አቅርቦት ችግር በመኖሩ መድኃኒት በራሳቸው ወጪ የሚገዙ በመሆኑ ችግር ውስጥ መሆናቸውን፣ የምግብ አቅርቦት በየጊዜው የሚመጣ ካለመሆኑ በተጨማሪ ጥራቱን የጠበቀ አለመሆኑን፣ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ አቅርቦት አለመኖሩን፣ መጠለያ ጣቢያው ግቢም ሆነ መጸዳጃ ቤቱ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አለመሆኑንና ልዩ ትኩረትና ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተፈናቃዮች የተለየ አቅርቦት አለመኖሩን ፣ተፈናቃዮች መሆናቸውን የሚገልጽ መታወቂያ ያላቸው መሆኑን፣ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በመጠለያ ጣቢያው በተዋቀሩ የሰላም ኮሚቴዎች እንደሚፈታ እና በአቅራቢያቸውም የጸጥታና የፍትህ አካላት መኖራቸውን ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ለማወቅ ችሏል::

በተጨማሪም ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያው ከገቡ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደመጡበት ለመመለስ ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን ኢሰመጉ ለማወቅ ችሏል::

4.2. ግብርና ግቢ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በወልድያ ከተማ ጉባ ላፍቶ ወረዳ የሚገኝ ሲሆን በውስጡም 79 ሴት እና 70 ወንድ በድምሩ 149 ተፈናቃዮችን ይዟል። በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች በ 2013 ዓ.ም ከኦሮምያ ክልል ከተለያዩ የወለጋ ዞኖች በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ናቸው፡ ፡ በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ 10 ድንኳኖች ያሉ ሲሆን በአንድ ድንኳን ውስጥ በአማካኝ 20 ሰዎችን ይይዛል።

ተፈናቃዮች ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸው መስተጋብር ሰላማዊ መሆኑን እና በአካባቢው ካለው ማህበረሰብ ጋር ጥሩ ማህበራዊ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን፣ መጠለያ ጣቢያው ባለበት አካባቢ የጸጥታና የፍትህ አካላት ያሉ ቢሆንም በክልሉ ባለው የጸጥታ ችግር ምክንያት መጠለያ ጣቢያው ያለበት አካባቢ ከስጋት ነጻ አለመሆኑን፣ የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ በ 3 ወር 15 ኪሎ ግራም ስንዴ በነብስ ወከፍ የሚቀርብ ቢሆንም በቂ አለመሆኑን እና በመጠለያ ጣቢያ ውስጥ የህክምና መስጫ ተቋም የሌለ ሲሆን ተፈናቃዮች የጤና እክል ሲያጋጥማቸው በአካባቢው ባለው የጤና ተቋም የህክምና እርዳታ እንደሚያገኙ፣ የፍራሽ ፣ብርድልብስ እንደገቡ አካባቢ የተሰጣቸው ቢሆንም ያለቀ መሆኑን፣ የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ አቅርቦት አለመኖሩን፣የመጠለያ ጣቢያው ጠባብ እና የተጨናነቀ መሆኑን እንዲሁም ህጻናት በአካባቢያቸው በሚገኝ ትምህርት ቤት ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው እንደሚማሩ እና ልዩ ትኩረትና ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተፈናቃዮች የተለየ ድጋፍ አለመኖሩን፣ ተፈናቃዮች መሆናቸውን የሚገልጽ መታወቂያ ያላቸው መሆኑን፣ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በመጠለያ ጣቢያው በተዋቀሩ የሰላም ኮሚቴዎች የሚፈታ መሆኑን እና በአካባቢያቸውም የአካባቢው ፖሊስ ጣቢያ ያለመሆኑን፣በተጨማሪም ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያው ከገቡ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደመጡበት ለመመለስ ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

4.3. ላም እርባታ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በወልድያ ከተማ 06 ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን በውስጡም 51 ሴት እና 47 ወንድ በድምሩ 91 ተፈናቃዮችን ይዟል። በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች በ 2013 ዓ.ም ከኦሮምያ ክልል ከተለያዩ የወለጋ ዞኖች በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ናቸው። ወደመጠለያው ሲገቡ የተመዘገቡ መሆኑን እና በመንግስት የተሰራው መጠለያ ጣቢያ በቂ ባለመሆኑ ከብት ይረባበት የነበረውን ቦታ በማጽዳት እየኖሩ መሆኑን፣ ነገር ግን መጠለያ ጣቢያው የተጨናነቀና ለመኖሪያ ምቹ አለመሆኑን፣ በአካባቢው ተንቀሳቅሰው ለመስራት የሚያስችላቸውን መታወቂያ የጠየቁ ቢሆንም ማግኘት አለመቻላቸውን ገልጸዋል። የምግብ አቅርቦት በአማካኝ በ 3 ወር በነብስ ወከፍ 15 እንደሚሰጣቸው የሚመጣው እህልም ጥራቱን ያልጠበቀ እና በብዛት የሚመጣው እህል የነቀዘ መሆኑን፣ ህክምናን በተመለከተ በአካባቢው ባለ ጤና ጣቢያ ነጻ

የህክምና አገልግሎት እያገኙ መሆናቸውን፣ ትምህርትን በተመለከተ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው መደበኛ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ሲሆን የመማሪያ ቁሳቁስ በበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንደሚቀርብ ለማወቅ ተችሏል። በመጠለያ ጣቢያው ግጭትና አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በተመረጡት ኮሚቴዎችና በፖሊስ እንደሚፈቱ እንዲሁም የፍትህ ተቋማት ለተፈናቃዮቹ ተደራሽ በሆነ መልኩ በአካባቢያቸው የሚገኝ መሆኑን፣ የፍራሽ፣ ብርድ ልብስ እና አንሶላ በ2014 ዓ.ም የተሰጣቸው ቢሆንም ያረጀና አገልግሎት የማያሰጥ መሆኑን፣ ለሴቶች የንጽህና መጠበቂያ በየወሩ የሚቀርብ መሆኑን፣ ለህጻናት የሚሆን የተለየ የምግብ አቅርቦት አለመኖሩን እንዲሁም ምግብን በተመለከተ ወቅቱን ጠብቆ እንደማይቀርብላቸው እንዲሁም ጥራቱን የጠበቀ አለመሆኑን ነገር ግን ከግብረ ሰናይ ድርጅቶች የገንዘብ እርዳታ ማግኘታቸውን እና መጠለያ ጣቢያው ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አለመሆኑን፣በተጨማሪም ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያው ከገቡ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደመጡበት ለመመለስ ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን ኢሰመጉ በምልከታው ወቅት ለማወቅ ችሏል።

በሌላ በኩል በወልድያ ከተማ ከመጠለያ ጣቢያ ውጪ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩ ተፈናቃዮች ያሉ ሲሆን ይህም የሆነው ተፈናቅለው በመጡበት ወቅት ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው መኖር የጀመሩ እና ልጆቻቸውን ማስተማር የጀመሩ በመሆኑ ሲሆን ጃራ መጠለያ ጣቢያ እንዲገቡ ሀሳብ ቀርቦ የነበረ ቢሆንም የልጆቻቸው የትምህርት ሁኔታን ከግምት ውስጥ በማስገባት ባሉበት እንዲቆዩ መደረጉን እና መንግስታዊ ያልሆኑ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች የገንዘብ እርዳታ እና 15 ኪሎ በቆሎ በነፍስ ወከፍ ከመንግስት የሚደረግ ድጋፍ ቢኖርም ጊዜውን ጠብቆ የሚደረግ ባለመሆኑ ችግር ውስጥ መሆናቸውን እና መጠለያ ጣቢያ ውስጥ የገቡ ባለመሆናቸው እንደተፈናቃይ ተቆጥረው በሚገባው ልክ እርዳታ እያገኙ አለመሆኑን እንዲሁም ተፈናቃዮች በቤተክርስቲያን፣ በመስጊድና አንዳንዶቹም ቤት ተከራይተው እየኖሩ የሚገኙ ቢሆንም የቤት ኪራይ ለመክፈል መቸገራቸውን ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት በመንግስት የሚደረግው ጥረትም አነስተኛ እንደሆነ ለኢሰመጉ ገልጸዋል።

4.4. ቀበሮ ሜዳ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በማዕከላዊ ጎንደር ዞን ጎንደር ከተማ በቅርብ ርቀት አዘዞ የከተማዉ የሚገኘዉ ሲሆን በውስጡ 630 እማወራ፣ 721 አባወራ እና 269 ህጻናት በአጠቃላይ 1,620 ተፈናቃዮች ይገኛሉ።

በጎንደር ከተማ የሚገኙት ተፈናቃዮች ከሃገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ማለትም ከወለጋ፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን እና በሰሜኑ ጦርነት ወቅት ከትግራይ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በማንነታቸዉ ምክንያት የተፈናቀሉ ሲሆን ከወለጋና ከመተከል ዞኖች የተፈናቀሉት

ከመጠለያ ጣቢያ ዉጭ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው በከተማዉ የሚኖሩ ሲሆን ቀበሮ ሜዳ ተብሎ በሚጠራዉ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች ጥቅምት 24/2013 ዓ/ም በትግራይ ክልል በነበረው ጦርነት ምክንያት በህዳር እና ታህሳስ ወር 2013 ዓ.ም የተፈናቀሉ ናቸው::

የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ ተፈናቅለዉ እንደመጡ ለ3 ወር ያህል ከከተማዉ ነዋሪ ውጭ እርዳታ የሚሰጣቸዉ አካል ያልነበረ ሲሆን አሁንም ቢሆን የሚቀርበው እህል በነፍስ ወከፍ 15 ኪሎ ስንዴ ወይም በቆሎ ሲሆን ወቅቱን እና ጥራቱን የጠበቀ አለመሆኑን እና አንዳንድ በጎ አድራጊ ግለሰቦችና ድርጅቶች እገዛ እንደሚያደርጉላቸዉ ለማወቅ ተችሏል:: የንጽህና መጠበቂያ ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ ቁሳቁሶች በቂ አለመሆናቸዉን፣ ፍራሽ አንሶላና ብርድ ልብስ ወዲያዉ እንደመጡ ማለትም ከ 4 ዓመት በፊት አንዴ ብቻ ተሰጥቷቸው የነበረ መሆኑን፣ ከትምህርት ጋር ተያይዞ በመጠለያ ጣቢያዉ በቅርብ ርቀት በሚገኝ ነኛ ደረጃ ት/ቤት የሚማሩ መሆኑን እና የትምህርት መማሪያ ቁሳቁስ በዚህ የትምህርት አመት ያልተሰጣቸው መሆኑን እና በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ 2 ቆርቆሮ በቆርቆሮ በሆነ ከፍል ውስጥ መምህር ተቀጥሮላቸዉ ህጻናት እየተማሩ መሆኑን ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ለመመልከት ችሏል::

በአማራ ክልል ካለው የጸጥታ ችግር ጋር ተያይዞ መጠለያ ጣቢያው የሚገኝበት ቦታ ለደህንነት አስጊ መሆኑን በተለይም ደግሞ በመጠለያ ጣቢያው ቅርብ ርቀት የመንግስት የጸጥታ ሃይሎች ካምፕ ያለ ሲሆን በሌላ አቅጣጫ ደግሞ የፋኖ ሃይሎች በቅርብ ርቀት ላይ እንደሚገኙ በዚህም ግጭት ሲፈጠር ስጋት ውስጥ የሚጥል መሆኑን እንዲሁም መጠለያ ጣቢያ አጥር የሌለዉ በመሆኑ ለስርቆትና እገታ ተጋላጭ መሆናቸውን እና ለአካል ጉዳተኞችና ለህጻናት ምቹ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል:: በተጨማሪም ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያው ከገቡ እረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደመጡበት ለመመለስ ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን ኢሰመጉ ካሰባሰበው መረጃ ለመረዳት ችሏል ::



ጎንደር ቀበሮ ሜዳ የተፈናቃዮች መጠለያ

4.5. ሺ- መላኩ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በሰሜን ጎንደር ዞን ዳባት ከተማ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን መጠለያ ጣቢያው በውስጡ 23 ሴት፣ 18 ወንድ እና 5 ህጻናትን ጨምሮ 44 አካል ጉዳተኛ እና የአዕምሮ ህመም ያለባቸዉን ጨምሮ በድምሩ ከ 2040 በላይ ተፈናቃዮች ይገኛሉ፡፡ ከቆርቆሮ እና ከኬንዳ የተሰሩ 31 ብሎኮችና 142 ክፍሎች ያሉት ሲሆን በአማካይ 6 በ7 ሜትር ካሬ ስፋት ያላቸው ክፍሎች ውስጥ ከ 8 - 9 ሰዉ ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙት ተፈናቃዮች በትግራይ ክልል በነበረው ጦርነት ምክንያት በህዳር እና ታህሳስ ወር 2013 ዓ.ም ከትግራይ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች የተፈናቀሉ ሲሆን መጀመሪያ ላይ ሰሜን ጎንደር ደባርቅ ከተማ እንደቆዩ እና ከተወሰኑ ጊዜያት በኋላ ከደባርቅ ከተማ በቅርብ ርቀት ላይ ወደሚገኘዉ ዳባት ወረዳ ታላቅ መስክ ቀበሌ ሺመላኩ ተብሎ ወደሚጠራዉ መጠለያ ጣቢያ የገቡ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ በነፍስ ወከፍ 15 ኪሎ ግራም ስንዴ ወይም በቆሎ የሚቀርብ ሲሆን ይህም በአማካኝ ከ 2 እስከ 3 ወር ቆይቶ እንደሚሰጣቸውና ጥራቱን የጠበቀ አለመሆኑን፣ መጠለያ ጣቢያው ክፍሎች የተጨናነቁ መሆኑን፣ በክረመረት አብዘኛው ክፍል በሸራ የተሰራና በየጊዜው እድሳት ስለማይደረግለት ዝናብ የሚያስገባ መሆኑን፣ እንደመሆኑ ከንጽህና መጠበቂያ ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ ቁሳቁሶች በቂ አለመሆናቸዉ፣ ፍራሽ፣ አንሶላና ብርድ ልብስ ወደመጠለያ ጣቢያው በገቡ ወቅት አንድ ጊዜ ብቻ የተሰጣቸው መሆኑን፣ ህክምናን በተመለከተ በግብረሰናይ ድርጅት የተቋቋመ የጤና ማዕከል ያለ ቢሆንም ስራ ካቆመ አንድ አመት በመሆኑ ለጤናቸዉ አሳሳቢ መሆኑን፣ ትምህርትን በተመለከተ መጠለያ ጣቢያው ከከተማው ሩቅ በመሆኑ ልጆቻቸውን ከተማ ባሉ ት/ቤቶች ልከው ለማስተማር አዳጋች መሆኑን እና ለተማሪዎች የሚሰጣቸዉ የትምህርት መማሪያ ቁሳቁስ ከመስከረም 2017 ዓ/ም ጀምሮ የትምህርት መማሪያ አቅርቦት አለመኖሩን እና ለህጻናት ማቆያ የሚሆን የትምህርት መስጫ ማዕከል ባለመኖሩ ህጻናቱ ለከፍተኛ የስነ ልቦና ጫና እየደረሰባቸዉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል በክልሉ ባለው የፀጥታ ችግር ምክንያት መጠለያ ጣቢያዉ የሚገኝበት ቦታ ለደህንነት አስጊ መሆኑን እና መጠለያ ጣቢያውን ለመጠበቅ ተመድበዉ ሲሰሩ የነበሩት ጥበቃዎች በክልሉ ባለዉ ወቅታዊ ግጭት ምክንያት በመነሳታቸው ስጋት ውስጥ መውደቃቸውን፣ መጠለያ ጣቢያዉ የሚገኝበት ቦታ ለአካል ጉዳተኞችና ለህጻናት ምቹ አለመሆኑን፣ በአካባቢው የመጠጥ ውሃ ዕጥረት በመኖሩ እናቶች ውሃ ለመቅዳት ሲሄዱ ስድብና ጾታዊ ትንኮሳ እንደሚደርስባቸው በጉብኝቱ ወቅት ለኢሰመጉ ተገልጸለታል፡፡

መፈናቀላቸው ህጻናት ላይ ከፍተኛ የሆነ የስነልቦና ጫና ያደረሰ መሆኑን ተፈናቃዮቹ ሲገልጹ፡፡ ህጻናቱ በአፈር በሚጫወቱበት ጊዜ 2 ኪሎ አፈር ላንተ ውሰድ 3 ኪሎ አፈር ደግሞ ላንቺ ውሰጂ

በመባባል የሚጫወቱ ሲሆን ይህም እርዳታ አቅራቢ አካላት ለተፈናቃዮቹ በሚያከፋፍሉበት ወቅት ያዩትን ነገር እነሱ ደግሞ በአፈር ይህንን የእርዳታ ስነልቦና ይዘዉ እያደጉ በመሆኑ አስቸጋሪ ነዉ›› በማለት አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያው ከገቡ እረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደመጡበት ለመመለስ ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል፡፡





ዳባት ሺ መላኩ የሚገኘዉ የተፈናቃይ ማቆያ ጣቢያ የተወሰኑ ምስሎች

4.6. የወይንሸት ፣ ባቄሎ እና ቻይና ካምፕ መጠለያ ጣቢያ

እነዚህ መጠለያ ጣቢያዎች በደብረ ብርሀን ከተማ ይገኛሉ፡፡ የወይንሸት መጠለያ ጣቢያ በውስጡም 5,969 ሴት እና 5,634 ወንድ በአጠቃላይ 11,603 ተፈናቃዮች የያዘ ሲሆን በቻይና ካምፕ መጠለያ ጣቢያ ውስጥ 3,700 ሴት እና 3,300 ወንድ በድምሩ 7,000 ተፈናቃዮች ፣ በባቄሎ መጠለያ ጣቢያ ደግሞ 501 ሴት እና 836 ወንድ በአጠቃላይ 1337 ተፈናቃዮች የሚገኙ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 131 አካል ጉዳተኞች እንደሚገኙ ታውቋል፡፡ በእነዚህ መጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙ ተፈናቃዮች ከተለያዩ የኦሮምያ አካባቢዎች በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ሲሆን ተፈናቃዮች ለዘመናት ከኖሩበት አካባቢ ሲፈናቀሉ ንብረታቸው መውደሙን፣ ጎረቤቶቻቸው እና ዘመዶቻቸው የነበሩ በርካታ ሰዎች መገደላቸውን እና የአካል ጉዳት መድረሱን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ተፈናቃዮች ወደ እነዚህ መጠለያ ጣቢያዎች ከገቡ ከአራት አመታት በላይ መሆኑን፣ የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ በአማካኝ በ 2 እና በ 3 ወር ጊዜ ውስጥ በነፍስ ወከፍ 15 ኪሎ ግራም በቆሎ ወይም ስንዴ የሚሰጥ ቢሆንም በቂ እና ጥራቱን የጠበቀ ባለመሆኑ ለችግር መዳረጋቸውን፣ በመጠለያ ጣቢያው የመኝታ አዳራሾቹ ውስጥ በርካታ ሰዎች የሚኖሩ በመሆኑ ለመኖር ምቹ አለመሆኑን፣ ምግብ የሚያበስልቱም ፍራሻቸው አጠገብ በመሆኑ ለመንቀሳቀስ አስቸጋሪና የተጨናነቀ መሆኑን እና መጠለያዎቹ የተሰሩት ከሸራ በመሆኑ በጸሐይ፣ ዝናብ እና በነፋስ ምክንያት የተቀደዱ በመሆናቸው በክረምት ወቅት ለከፍተኛ ችግር እንደሚጋለጡ ለመረዳት ተችሏል፡፡

የህክምና አቅርቦትን በተመለከተ በመጠለያ ጣቢያዎቹ የህክምና ተቋም ያለ ቢሆንም የመድሀኒት

እጥረት መኖሩን እና ሪፈር ተብለው ወደሆስፒታል ሲላኩ መድሃኒት ከውጭ እንዲገዙ እንደሚደረግ ፣ በባቄሎ መጠለያ ጣቢያ ውስጥ በቂ የመጸዳጃ ቤቶችና የውሃ አቅርቦት ያለ ቢሆንም በሌሎቹ መጠለያ ጣቢያዎች አለመኖሩን እንዲሁም ለትምህርት የደረሱ ህጻናት የመደበኛ ደረጃ ትምህርት እየተማሩ መሆኑን ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለማወቅ ችሏል፡፡ የተወሰኑ ተፈናቃዮችን ወደ ተፈናቀሉበት አካባቢ የተመለሱ ቢሆንም የአካባቢው የፀጥታ ሁኔታ በለመሻሻሉ የተወሰኑ ተፈናቃዮች ለዳግም መፈናቀል የተዳረጉ መሆኑን እና ከዛ በኋላ ግን መልሶ ለማቋቋም ወይም ከመህበረሰብ ጋር ለማቀላቀል እና ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት ዝቅተኛ መሆኑን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለማወቅ ችሏል፡፡

4.7. ገራዶ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በደቡብ ወሎ ዞን በደሴ ዙሪያ ወረዳ ገራዶ ከተማ የሚገኝ ሲሆን በዚህ መጠለያ ጣቢያ 302 ሴት እና 232 ወንድ በድምሩ 534 ተፈናቃዮች ይገኛሉ ፡፡ እነዚህ ተፈናቃዮችም ከኦሮሚያ ክልል ወለጋ እና አካባቢው ከሚገኙ ወረዳዎች በ 2013 ዓ.ም መጨረሻ በተከሰተ ግጭት የተነሳ ከመኖሪያ ቀያቸው በአካባቢው በሚንሳቀሱ ታጣቂ ሃይሎች የተፈናቀሉ ናቸው፡፡

ተፈናቃዮች እዚህ መጠለያ ጣቢያ እንደገቡ አካባቢ ከአካባቢው ማህበረሰብ ፣ ከመንግስት እና ከተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የተለያዩ ድጋፎች ይቀርብላቸው የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በነፍስ ወከፍ 15 ኪሎ በቆሎ በ 3 ወር የሚቀርብ ቢሆንም ጥራቱን የጠበቀና በቂ አለመሆኑን፣ የህፃናት አልሚ ምግብ በቂ ባይሆንም አቅርቦት መኖሩን፣ የንፅህና መጠበቂያ አቅርቦት አለመኖሩን፣ የብርድ ልብስ፣ ፍራሽ እና አንሶላ ከ 4 አመት በፊት የተሰጣቸው በመሆኑ ማለቁንና አቅርቦትም አለመኖሩን፣ መታወቅያ፣ የልደት ሰርተፊኬት ያልተሰጣቸው በመሆኑ በነጻነት ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ አለመቻላቸውን በአካባቢውም ከለው የጸጥታ ችግር ጋር ተያይዞ በዘህው አካባቢ የሞቱ ዘመዳቻውን እንኳን ሂዳለ መቅበር እንደማይችሉ ስራም ወደሊላ ቦታ ተንቀሳቅሰው ለመስራት መቸገራቸውን እና የህክምና አገልግሎትን በተመለከተ በአካባቢው ባለው የጤና ተቋም አገልግሎቱን እያገኙ ቢሆንም የመድሀኒት አቅርቦት ባለመኖሩ ለከፍተኛ ችግር እየተዳረጉ መሆናቸውን ኢሰመጉ ለማወቅ ችሏል፡፡ መጠለያ ጣቢያው ተፈናቃዮች በገቡ ወቅት በደሴ ዙሪያ ወረዳ ስር ይገኝ የነበረ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በደሴ ከተማ መስተዳደር ስር በመካለሉ የከተማው መስተዳደሩ መጠለያ ጣቢያው የሚገኝበትን ቦታ ለባለሀብት የሸጠው በመሆኑ ባለሀብቱ የተወሰኑ የመጠለያ ክፍሎችን ማፍረሱንና ተፈናቃዮቹም ተነሱ ተብሎ የተነገራቸው ቢሆንም የአካባቢው የመንግስት አካላት እነዚህን ተፈናቃዮች ወደ ሌላ ቦታ ለመቀየር ምንም አይነት ጥረት እያደረገ አለመሆኑን ይህም ተፈናቃዮቹን ስጋት ላይ የጣላቸው ጉዳይ መሆኑን ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ለማወቅ ችሏል፡፡ ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያው ረጅም ጊዜ የሆናቸው ቢሆንም ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት ወይም ለማቋቋም

የሚደረግ ተገቢ ጥረት አለመኖሩን እና የተፈናቀሉበት ቦታ የፀጥታ ሁኔታ ባልተሻሻለበት ሁኔታ እንዲመለሱ ከመግለጽ ውጭ በጥናት የታገዘ የአካባቢውን ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት የሚደረገው እንቅስቃሴ ደካማ መሆኑን እና መልሶ ማቋቋምን በተመለከተ ከተፈናቃዮች ጋር ውይይት እንደማያደረጉ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ኢሰመጉ የሚመለከታቸውን የመንግስት ባለድርሻ አካላት ለማናገር ሙከራ አድርጎ የነበረ ሲሆን ዘላቂ መፍትሔን እና ተፈናቃዮች ያሉበትን ወቅታዊ ሁኔታ አስመልክቶ በቂ ምላሽ ማግኘት አልተቻለም፡፡

4.8. ቻይና ካምፕ/ደጋን መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በአማራ ክልል በደቡብ ወሎ ዞን ቃሉ ወረዳ ደጋን ከተማ በቅርብ ርቀት የሚገኝ ሲሆን በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ 430 ሴት 452 ወንድ እና 850 ህፃናት በድምሩ 1,905 ተፈናቃዮች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ተፈናቃዮች በ 2013 ዓ.ም ከኦሮሚያ ክልል ከተለያዩ የወለጋ ዞኖች በነበረ ብሔርን መሰረት ያደረገ ግጭት እንዲሁም በሶማሌ እና በአፍር ክልል ኢሳ ጎሳ መካከል በነበረው የድንበር ይገባኛል ጥያቄ በተነሳ ግጭት የተፈናቀሉ ሲሆን በመንግስት ተገቢውን ጥበቃ ባለመደረጉ በግጭቱ ወቅት ተፈናቃዮች የሞት፣ የአካል ጉዳት እና የንብረት ውድመት ደርሶባቸዋል፡፡ ይህ መጠለያ ጣቢያ የቻይና መንገድ ስራዎች የሰሩትና ሲጠቀሙበት የነበረ በመሆኑ ክፍሎቹ የተሻለ አደረጃጀት ያላቸው መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የተወሰኑት ግን በሸር የተሰራ መተለያ ውስጥ ሲሆን የሚኖሩት ሽራው ያረጀና ጠባብ ነው ፡፡ ተፈናቃዮች ወደ መጠለያ ጣቢያ እንደገቡ ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች በተከታታይነት ድጋፎች ይቀርቡላቸው የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ በቂ እና ጥራቱን የጠበቀ ባይሆንም በ 4 ወር በነብስ ወከፍ 15 ኪሎ ግራም በቆሎ የሚቀርብ መሆኑን ፣የፍራሽ ፣ብርድልብስ እንደገቡ የተሰጣቸው ቢሆንም እረጅን ጊዜ የሆነው በመሆኑ ያረጀ መሆኑን፣ ለህፃናት የአልሚ ምግብ አቅርቦት የሊለ መሆኑን ፣ የሴቶች የንፃህና መጠበቅያ አልፍአልፍ ግብረሰናይ ድርጅቶች ይሰጦቸው የነበር ቢሆንም አሁን ላይ ግን የተቋረጠ መሆኑን፣ በግቢው ውስጥ በግብረ ሰናይ ድርጅት የተቋቋመ የጤና ተቋም የነበረ ቢሆንም ይህ ክትትል ከተደረገበት አንድ ሳምንት በፊት ለቀው መውጣታቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ትምህርትን በተመለከተ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው መደበኛ ትምህርት የሚከታተሉ ቢሆንም ትምህርት ቤቱ ከመጠለያ ጣቢያው ሩቅ በመሆኑ ትራንስፖርት መክፈል የሚችሉ ወላጆች ልጆቻቸውን ቢያስተምሩም፤ የትራንስፖርት ክፍያ መክፈል የማይችሉ ወላጆች ልጆቻቸውን ልከው ማስተማር እንዳይችሉ ምክንያት ሆኗል፡፡ በመጠለያ ጣቢያው የኤሌክትሪክ አቅርቦት ባለመኖሩ ምክንያት ምግብ ለማብሰል ይረዳቸው ዘንድ በአካባቢው እንጨት ለመልቀም በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር አለመግባባት እየፈጠረባቸው መሆኑን ኢሰመጉ በጉብኝቱ ወቅት ለማወቅ ችሏል፡፡ ከአፋር ክልል አንጻራዊ ሰላም ያለ በመሆኑ ተፈናቃዮች መመለስ እንደሚፈልጉና በሚመለከተው የመንግስት አካል ቃል ቢገባላቸውም

ሳይመለሱ እና ዘላቂ መፍትሄ ሳይሰጣቸው 4 አመታትን ማስቆጠራቸውን በተመሳሳይ ከወለጋ የተለያዩ ዞኖች የመጡ ተፈናቃዮችም ዘላቂ መፍትሄ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ቢጠይቁም ምንም አይነት መፍትሄ እየተሰጣቸው አለመሆኑን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለማወቅ ችሏል።

4.9. መዲና መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በአማራ ክልል በደቡብ ወሎ ዞን አርጎባ ወረዳ መዲና ከተማ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን በዚህ መጠለያ ጣቢያም 334 ሴት እና 482 ወንድ በድምር 816 ተፈናቃዮች ይገኛሉ። እነዚህ ተፈናቃዮች ከኦሮሚያ ክልል ከተለያዩ የወለጋ ዞኖች ና ወረዳዎች በ 2013 እና 2014 ዓ.ም በአካባቢው በሚንቀሳቀሱ የታጠቁ አካላት በተነሳው ግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ናቸው። መጠለያ ጣቢያው የሚገኝበት አካባቢ ከዋናዉ መንገድ ብዙ ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ የሚገኝ በመሆኑ እና መንገዱም የጠጠር(ፒስታ) መንገድ በመሆኑ ለሰብዓዊ ድጋፍ አቅርቦት ችግር መፍጠሩን በተለይም የምግብ አቅርቦት ጊዜውን ጠብቆ የማይደርሳቸው መሆኑን እና የሚሰጠውም እህል በነብስ ወከፍ 15 ኪሎ በቆሎ ሲሆን ጥራቱን የጠበቀ አለመሆኑን፣የፍራሽ ብርድ ልብስ አቅረቦት እንደገቡ የተሰጣቸው ቢሆንም አሁን ላይ ያረጀ መሆኑን፣ የሴቶች ንፃህና መጠበቂያ አቅርቦት የሌለ መሆኑን፣ መደበኛ ትምህርት ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው የሚማሩ ቢሆንም ከነዋሪው እኩል መዋጮ አዋጡ እንደሚባሉ በዚህም የተነሳ አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸውን ለማስተማር ችግር እንደሆነባቸው፣ የትምህርት ቁሳቁስ አቅረቦት የሌለ መሆኑን፣ መጠለያ ጣቢያው ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አለመሆኑን ፣መንገዱ ምቹ ባለመሆኑ እንደሌሎች የመጠለያ ጣቢያዎች ግብረ ሰናይ ድርጅቶች በብዛት ወደ መጠለያ ጣቢያው እንደማይገቡ እና በመጠለያ ጣቢያው ከመጠለላቸው ውጭ የሚደረግላቸው ድጋፍ ዝቅተኛ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። የህክምና አቅርቦትን በተመለከተ በአካባቢው ባለ ጤና ጣቢያ የህክምና አገልግሎት የሚያገኙ ቢሆንም የመድሃኒት አቅርቦት እጥረት መኖሩን ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያው ከገቡ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደመጡበት ለመመለስ ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል።

4.10. ኮሌጅ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በሰሜን ወሎ ዞን ወልድያ ከተማ ኮሌጅ ተብሎ በሚጠራ ክፍል የሚገኝ ሲሆን በዚህ መጠለያ ጣቢያ 57 ሴት እና 85 ወንድ በድምሩ 142 ተፈናቃዮች ይገኛሉ። በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች ከሃገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ማለትም ከኦሮሚያ ክልል ወለጋና ሸዋ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከልና ካማሽ ዞኖች፣ ሱማሌ ክልል እና በሰሜኑ ጦርነት ወቅት ደግሞ ከትግራይ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች የተፈናቀሉ ናቸው። ዓለም አቀፍም ሆነ አገር በቀል ረጅ ድርጅቶች ከዚህ በፊት ሲያቀርቡ የነበረውን የንጽህና መጠበቂያና መሰል ቁሳቁሶች እርዳት ሙሉ በሙሉ መቆሙ እና የምግብ አቅርቦት በነፍስ ወከፍ 15 ኪሎ

ግራም እህል በአማካኝ ከ 3 እስከ 4 ወር የሚቀርብ ቢሆንም ጥራቱን የጠበቀ ባለመሆኑ ከፍተኛ ለሆነ የምግብ እጥረት መጋለጣቸውን፣ የፍራሽ ፣ብርድ ልብስ የተሰጣው ቢሆንም እረጅም ጊዜ የሆነው በመሆኑ ያረጀ መሆኑን፣ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ለአካል ጉዳተኞች ፣ለህፃናትና እድሜያቸው ለገፋ አረጋዊያን የተለየ ድጋፍ አለመኖሩን እና በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ የመፀዳጃ ቤት የሌለው በመሆኑ ለከፍተኛ ችግር መጋለጣቸውንና በተለይ ሴቶች መጸዳጃ ባለመኖሩ ራቅ ያለ ቦታና ምሽትን የሚመርጡ በመሆኑ ለተለያዩ ጥቃቶች እየተጋለጡ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።። በሌላ በኩል በመጠለያ ጣቢያዉ ቅርብ ርቀት ላይ የመንግስት የጸጥታ ሃይሎች ካምፖች ያሉ ሲሆን ግንቦት 14 ምሽት አካባቢ ከወልድያ ስታዲየም አካባቢ በተተኮሰ ከባድ መሳሪያ ምክንያት የተወሰኑ መጠለያ ጣቢያዎች ላይ ተፈናቃዮች ከዉስጥ በነበሩበት ወቅት ቀላል ጉዳት ማድረሱንና የተሰማዉን የከባድ መሳሪያ ተኩስ ምክንያት በማድረግም በዕለቱ በማቆያ ጣቢያዉ አካባቢ ከፍተኛ የሆነ የተኩስ ልዉዉጥ የነበረ በመሆኑ በተፈናቃዮች ላይ ከፍተኛ የሆነ የደህንነት ስጋትና ድንጋጤ ፈጥሮ የነበረ መሆኑን እና በመጠለያ ጣቢያው ከፍተኛ የደህንነት ስጋት መኖሩን፣ ዘላቂ መፍትሄን እና ወደ ነበሩበት አካባቢ የመመለስ ስራን በተመለከተ የተሞከሩ ነገሮች ቢኖሩም በቂ እና የሰላሙ ሁኔታ አስተማማኝ ባለመሆኑ ለመመለስ ፈቃደኛ አለመሆናቸዉን እና ባሉበት አካባቢ የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ የሚያስችላቸውን ዘላቂ መፍትሄ ሊሰጣቸው የሚገባ መሆኑን እንዲሁም መጠለያ ጣቢያው ፈርሶ ለልማትና ለኢንቨስትመንት ሊሰጥ ነዉ በሚል ተፈናቃዮች ለፍርሃትና ለስነ ልቦና ጫና መዳረጋቸውንም አስረድተውናል።።

4.11. አሏሬ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኘዉ በሰሜን ወሎ ዞን ራያ ቆቦ ወረዳ አሏሬ ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን ሴት 370፣ ወንድ 330 እና ከ 30 እሰከ 40 የሚሆኑ አካል ጉዳተኞች በድምሩ ከ 700 በላይ ተፈናቃዮች ይገኛሉ።። በዚህ መጠለያ የሚገኙ ተፈናቃዮች ከ 2010 ዓ/ም ጀምሮ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተለይም ከተለያዩ የወለጋ ዞኖች እና ከመተከልና ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ማንነትን መሰረት ባደረግ ጥቃት ምክንያት የተፈናቀሉ ናቸው።። መጠለያ ጣቢያ ዉስጥ 4 ሼዶች የሚገኙ ሲሆን በአንድ ሼድ ውስጥ በአማካኝ ከ30- 40 ተፈናቃዮች የሚኖሩ ሲሆን አንዳንድ ተፈናቃዮች ደግሞ ትንንሽ ቤቶችን በመጠለያው ዙሪያ በመስራት ይኖራሉ።። መጠለያ ጣቢያው የተጨናነቀ እና ለኑሮ ምቹ አለ መሆኑን፣ የምግብ አቅርቦት ጊዜውን ጠብቆ እንደማያቀርብላቸው እና ጥራቱንም የጠበቀ አለመሆኑን ፣ የሴቶች ነንፃህና መጠበቂያ አቅርቦት የሊለ መሆኑን ፣ፍራሽ ፣ብርድ ልብስ እንደመጡ የተሰጣቸው ቢሆንም ያረጀ መሆኑን፣ መጠለያ ጣቢያዉ ከከተማም ሆነ ከሌሎች የወረዳዉ ነዋሪዎች ከሚኖሩበት ወጣ ያለ በመሆኑ የጤና እና የትምህርት አገልግሎትን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት የተቸገሩ መሆኑን እና የቀበሌዉ ነዋሪዎችም ቦታው የኛ ነው ተነሱ በሚል አልፎ አልፎ ትንኮሳዎች መኖራቸውን እንዲሁም የኤሌክትሪክ አገልግሎት ባለመኖሩ ሴቶች የማገዶ እንጨት ለመልቀም ሲወጡ ለጾታዊ ጥቃት ተጋላጭ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል።። የህፃናት ትምህርትን በተመለከተ ከሰሜኑ ጦርነት በኋላ

ምንም አይነት የትምህርት አገልግሎት አለመኖሩንና ከሶስት ዓመት በላይ ህፃናት ከትምህርት ገበታ ውጭ መሆናቸውን፣ ተፈናቃዮች የጠፋባቸውን ማንነታቸውን የሚገልፅ መታወቂያ፣ የህፃናት የልደት ካርድና ሌሎች መሰረታዊ ማስረጃዎች ለማግኘት መቸገራቸውን፣ በተጨማሪም ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያው ከገቡ እረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደመጡበት ለመመለስ ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል።

4.12. መርሳ ከተማ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በሰሜን ወሎ ዞን መርሳ ከተማ 03 ቀበሌ ዉስጥ የሚገኝ ሲሆን 170 ሴት እና 194 ወንድ በድምሩ 364 የሚገኙ ሲሆን ከ 160 በላይ ከ 18 አመት በታች የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ናቸው። መጠለያ ጣቢያው ቀደም ሲል የአማራ ልዩ ሃይል ካምፕ የነበረ ሲሆን አሁን ላይ ለተፈናቃዮች እንደ ጊዜያዊ ማቆያ ጣቢያ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል። በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች ከ 2013 ዓ.ም ጀምሮ ከወለጋ የተለያዩ አካባቢዎች በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ናቸው። የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአይነት/ በቆሎ፣ ዘይት፣ ክክና የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ እንዲሁም በብር ድጋፍ ሲያደርጉላቸው የነበረ ሲሆን ኢሰመጉ ጉብኝት ባደረገበት ወቅት እርዳታ እያገኙ አለመሆኑን፣ ከከተማዉ ማህበረሰብ ጋር ያላቸዉ መስተጋብር አዎንታዊ ቢሆንም አልፎ አልፎ መድሎና መገለል መኖሩን፣ ህጻናት ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው መደበኛ ትምህርት የሚያገኙ ቢሆንም ለትምህርት የሚያገለግሉ እስክርቢቶ እና ደብተር እንዲሁም ዩኒፎርም ለማግኘት ጉድለት መኖሩን እና ት/ቤት ዉስጥ የተፈናቃይ ልጅ እየተባሉ የሚጠሩ በመሆኑ የስነ ልቦና ጫና እያደረሰባቸው መሆኑን ፣ የጤና አገልግሎትን በተመለከተ ከወባ በሽታ መከላከያ በስተቀር ሙሉ የህክምና አገልግሎት ማግኘት ከባድ መሆኑን እና በተለይ ከባድ የህምም ዓይነቶች ካንሰር፣ግፊትና ሌሎችም ተፈናቃዮች በግል ወጪያቸዉ እንደሚታከሙ ለማወቅ ተችሏል።

በተጨማሪም ከተማዉ ሞቃታማ የአየር ጸባይ ያለዉ በመሆኑ እና የመጠለያ ጣቢያው መኖሪያ ክፍሎቹም የተጨናነቁ በመሆናቸው ለተስቦ በሽታ ተጋላጭ መሆናቸውን፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ባለመኖሩ ሴቶች ምግብ ለማብሰል የሚያስችላቸውን የማገዶ እንጨት ለመልቀም በሚወጡበት ወቅት ለተለያዩ አይነት የጾታዊ ጥቃት፣ ዛቻና ማስፈራራት ተጋላጭ መሆናቸውን እና በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት በድጋሚ የተፈናቀሉ በመሆናቸው ስነልቦናቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳደረባቸው መሆኑን፣በተጨማሪም ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያው ከገቡ እረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደመጡበት ለመመለስ ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል።

4.13. ጃራ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በሰሜን ወሎ ዞን ሃበሩ ወረዳ ድሌ ሮቃ ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን 4,076 ሴት ፣ 4,752 ወንድ እና 837 ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት በድምሩ 9,665 ተፈናቃዮች ይገኛሉ፡ ፡ መጠለያ ጣቢያው ከሸራ የተሰሩ 336 ቤቶች ያሉት ሲሆን አንድ ቤት በአማካኝ 6 ከፍሎች ያለዉና በአንድ ክፍል ዉስጥ ደግሞ ከ4-6 የሚደርሱ አባወራዎች/እማወራዎች ይኖሩበታል፡ ፡ ይህም በመሆኑ መጠለያ ጣቢያው የተጨናነቀና ለኑሮ ምቹ አያደለም፣ የምግብ አቅርቦት ጊዜውን ጠብቆ እንደማያቀርብ እና ጥራቱን የተበቀ አለመሆኑን፣ ፍራሽ፣ ብርድልብስ እንደገቡ ተሰጣቸው ቢሆንም እረጅም ጊዜ የሆነው በመሆኑ ያረጀ እና አገልግሎት የማያሰጥ መሆኑን፣ መጠለያ ጣቢያው ከአፋር ክልል በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝ በመሆኑ መጠለያ ጣቢያው የሚገኝበት ቀበሌ ነዋሪዎች ከአፋር ተወላጆች ጋር በግጦሽ መሬት እና በሌሎች ምክንያቶች በሚነሱ ግጭቶች ተፈናቃዮች ላይ ጉዳት እየደረሰ መሆኑን፣ አካባቢው ሞቃታማ በመሆኑ ምቹ አለመሆኑንና ለተለያዩ በሽታዎች ተጋላጭ መሆናቸውን እና መጠለያ ጣቢያው ከከተማ ሩቅ በመሆኑ የትምህርትና የጤና አገልግሎትን ጨምሮ ሌሎች አቅርቦቶች እንዳይኖር ተግዳሮት መሆኑን እንዲሁም የምግብ ማብሰያ የኤሌክትሪክ አገልግሎትና የውሃ አቅርቦት ችግር በመኖሩ ሴቶች የማገዶ እንጨት ለመልቀም ወደ ጫካ በሚሄዱበት ወቅት ፆታዊ ጥቃት ተጋላጭ መሆናቸውን፣ በተጨማሪም ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያው ከገቡ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደመጡበት ለመመለስ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል።።

4.14. ማይቡሊት መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በአማራ ክልል በዋግምህራ ብሔረሰብ ዞን ሰቆጣ ከተማ የሚገኝ ሲሆን 28 አባወራ እና 29 እማወራ በአጠቃላይ 57 ተፈናቃዮች ይገኛሉ።። በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች በግጭት ምክንያት ከኦሮምያ ክልል፣ ከትግራይ ክልል እና ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ በለው ጊዜ ከተለያዩ አካባቢዎች የተፈናቀሉ ሲሆን በአካባቢው ታጥቀው የሚንቀሳቀሱ አካላት ማንነትን መሰረት ያደረገ ጥቃት የደረሰባቸው መሆኑን፣ በግጭቱ ወቅት ንብረታቸው መውደሙን እና አንዳንድ የቤተሰባቸውን አካላት ማጣታቸውን እንዲሁም የአካባቢው የፀጥታ አካላት ተገቢውን ጥበቃ እና ከለላ ሊሰጣቸው ባለመቻላቸው የተፈናቀሉ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።።

ይህ መጠለያ ጣቢያ በአንድ ድንኳን የተሰራ ሲሆን ክፍሎቹ የተከፋፈሉ እና በአንድ ክፍል ውስጥ ከ 3 በላይ አባወራ/እማወር የሚኖሩበት በመሆኑ በጣም የተጨናነቀ እና ለመንቀሳቀስ አስቸጋሪ በመሆኑ ቀን ቀን የሚተኙበትን ፍራሽ በማንሳት ምግብ የሚያበስሉ መሆኑን፣ መፀዳጃ የሌለ በመሆኑ መቸገራቸውን በተለይ ሴቶች ለጾታዊ ጥቃት ተጋላጭ መሆናቸውን ፣ የውሃ አቅርቦት አለመኖሩን ፣ የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ የሚቀርበው እህል በቂ እና ጥራቱን

የጠበቀ ካለመሆኑም በተጨማሪ ከቀረበላቸው ከ4 ወር በላይ መሆኑን እና የሚሰጠው የእህል መጠን በነብስ ወከፍ ሳይሆን በአባወራ ወይም በእማወራ 25 ኪሎ እንደሆነ እና አንድ ቤተሰብ ያለውም ሆነ አምስት ቤተሰብ ያለው አባወራ/እማወር እኩል የሚሰጣቸው በመሆኑ የቤተሰብ ብዛት ያላቸው ለከፍተኛ ችግር መጋለጣቸውን ገልጸውልናል እንዲሁም የፍራሽ፣ ብርድልብስ እንደገቡ የተሰጣቸው ቢሆንም እረጅም ጊዜ የሆነው በመሆኑ ያረጀ መሆኑን ፣ከግብረሰናይ ድርጅት የተወሰነ የገንዘብ ድጋፍ የሚቀርብላቸው መሆኑን ገልጸውልናል።

የህክምና አቅርቦትን በተመለከተ ግብረሰናይ ድርጅት ሲቀርብ የነበረ ቢሆንም ኢሰመጉ ክትትል ባደረገበት ወቅት ግብረ ሰናይ ድርጅቱ የወጣ በመሆኑ የህክምና አገልግሎቱ መቋረጡን እና በዚህም ምክንያት ተፈናቃዮች ለከፍተኛ ችግር እየተዳረጉ መሆኑን ፣ ህጻናት ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው መደበኛ ትምህርት እየተከታተሉ መሆኑን እንዲሁም የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ አቅርቦት አለመኖሩን ፣በተጨማሪም ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያው ከገቡ እረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደመጡበት ለመመለስ ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል።

4.15. አበርገሌ መጠለያ ጣቢያ

ኢሰመጉ በአማራ ክልል በዋግህምህራ ብሔረሰብ ዞን አበርገሌ ወረዳ የሚገኙ ተፈናቃዮችን የነበኘ ሲሆን በዚህ አካባቢ የሚገኙት ተፈናቃዮች በሰሜን ኢትዮጵያ በነበረው ጦርነት ምክንያት ከተለያዩ አካባቢዎች ከ2013 ዓ.ም የተፈናቀሉ ሲሆን የፕሪቶሪያውን ስምምነት ተከትሎ አብዛኛው ተፈናቃይ ወደነበሩበት ቦታ የተመለሱ ሲሆን ከማይካድራ የተፈናቀሉ 2,661 ሴት፣ 2,481 ወንድ በአጠቃላይ 5,142 ተፈናቃዮች ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው በግላቸው ቤት ተከራይተው ይኖራሉ። እነዚህ ተፈናቃዮች በጦርነቱ ወቅት የመንግስት ሰራተኛ (ሹመኛ) ቤተሰቦች የነበሩ እና የተወሰኑ ወረዳዎች ደግሞ የትግራይ ኃይል በመባል በሚታወቀው የታጠቀ ቡድን ቁጥጥር ስር በመሆኑ የመንግስት ሰራተኛ ቤተሰብ የነበሩ በመሆናቸው ሊያጠቁን ይችላሉ በሚል ስጋት ወደመጡበት አካባቢ መመለስ አለመቻላቸውን ለማወቅ ተችሏል። እነዚህ ተፈናቃዮች አስቸኳይ ድጋፍ ብቻ የሚያገኙ መሆኑን፣ የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ ኤፍ ኤች ኢትዮጵያ(FH Ethiopia) በቀን 19/9/2017ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር FHE /HO/231/05/2025 በጻፈው ደብዳቤ ካሁን በፊት ሲሰጥ የነበረው 15 ኪሎ በቆሎ ወይም ማሽላ ተቀንሶ 12 ኪሎ በቆሎ ወይም ማሽላ ለተረጂዎች እንዲሰጥ ተወስኗል። ይህ የምግብ መጠን ቅነሳ ግን የተፈናቀሉ (IDPs) ቤተሰቦችንና ከስደት የተመለሱትን የሚመለከት ባይሆንም የአበርገሌ ወረዳ ቅድመ ማስጠንቀቂያ እና አደጋ መከላከል ቢሮ በአማካኝ በ3 ወር አንድ ጊዜ 15 ኪሎ ማሽላ ይቀርብላቸው የነበረውን በማስቀረት ከ ኤፍ ኤች ኢትዮጵያ (FH Ethiopia) የተሰጠ ትእዛዝ ነው በማለት ከግንቦት 2016 ዓ.ም ጀምሮ 12ኪሎ እየተሰጣቸው መሆኑን የወረዳው አደጋ ስጋት ለኢሰመጉ በሰጠው መረጃ ለማወቅ ተችሏል። ነገር ግን ደብዳቤው ላይ የምግብ መጠን ቅነሳው የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን እንደማያካትት በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን በዚህም አግባብ ኢሰመጉ ከአበርገሌ ወረዳ ቅድመ

ማስጠንቀቂያ እና አደጋ መከላከል ቢሮ አሰራሩን ውይይት በማድረግ ምክረ ሃሳብ አቅርቧል፡፡

የህክምና አቅርቦት እንደማንኛውም ማህበረሰብ ጤና መድህን በማውጣት በአካባቢው በሚገኝ ጤና ጣቢያ የሚጠቀሙ መሆኑን፣ ህጻናት ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው መደበኛ ትምህርት የሚከታተሉ መሆኑን እና የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ እንደማይደረግላቸው እንዲሁም ተፈናቃዮች በግላቸው ተከራይተው ሲኖሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች አልፎ አልፎ ከሚያደርጉት የገንዘብ ድጋፍ ውጪ ከመንግስት ምንም አይነት ድጋፍ እየተደረገላቸው አለመሆኑን እና ከ5 ዓመት በላይ የሆናቸው ቢሆንም መልሶ ለማቋቋም በቂ እንቅስቃሴ እየተደረገ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

4.16. ሸዋሮቢት እና አጣዬ ከተማ መጠለያ ጣቢያ

በሸዋሮቢት ከተማ የሚገኘው መጠለያ ጣቢያ 339 ሴት እና 383 ወንድ በድምሩ 722 ተፈናቃዮን የያዘ ሲሆን በኤፍራታ ግድም ወረዳ አጣዬ ከተማ የሚገኝ መጠለያ ጣቢያ ሲሆን በውስጡ 8,674 ,ሴት እና 8,321 ወንድ በድምሩ 16,995 ተፈናቃዮችን ይዟል፡፡ በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች ሚያዚያ 8 ቀን 2013 ዓ.ም ከኤፍራታና ግድም ወረዳ በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ሲሆን ተፈናቃዮች ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር እርቅ የፈጸሙ ቢሆንም ወደነበሩበት ቦታ መመለስ አለመቻላቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በሁለቱም መጠለያ ጣቢያዎች የፍራሽ፣ ብርድ ልብስ እና አንሶላ አቅርቦት አለመኖሩን ፣ለሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ እና ለህጻናት የተለየ ምግብ አቅርቦት አለመኖሩን፣ለህጻናት የትምህርት አቅርቦት ባለመኖሩ የህጻናት ትምህርት ላይ ተግዳሮት ፈጥሯል፡፡ የምግብ አቅርቦት ጊዜውን ጠብቆ እንደማይሰጥ የሚቀርበው ምግብም ጥራቱን የጠበቀ አለመሆኑን፣ መጠለያ ጣቢያው በተለይ የሸዋሮቢት መጠለያ ጣቢያ በጣም የተጨናነቀ እና ለመንቀሳቀስ ምቹ አለመሆኑን፣ የሁለቱም ግቢ ለአካል ጉዳተኛ መቹ አለመሆኑን፣ በመጠለያ ጣቢያው የጸጥታና የሰላም ሁኔታን የሚቆጣጠር አካል የሌለ ቢሆንም አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በሀገር ሽማግሌዎች የሚፈታ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ መጠለያ ጣቢያው ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አለመሆኑን፣ ከፍተኛ የሆነ የመድሀኒት አቅርቦት እጥረት መኖሩን፣ በተጨማሪም ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያው ከገቡ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደመጡበት ለመመለስ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል፡፡

4.17. ምንጃር ሸንኮራ ወረዳ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በ ምንጃር ሸንኮራ ወረዳ አረርቲ ከተማ ውስጥ በሚገኙት የአረርቲ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤት እና መልካ ጅሎ ጊዜያዊ የመጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ከተለያዩ የኦሮምያ አካባቢዎች በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ናቸው፡፡ በመጠለያ ጣቢያዎቹ ውስጥ (አረርቲ ቴክኒክና ሙያ ት/ቤት፣ ልካ ጅሎ) 1,740 ተፈናቃዮች የሚገኙ ሲሆን በማህበረሰቡ ውስጥ መኖሪያ ቤት ተከራይተው የሚኖሩ 2,366 ተፈናቃዮች የሚገኙ መሆኑን

እና በአጠቃላይ በምንጃር ሸንኮራ ወረዳ ውስጥ 4,101 ተፈናቃዮች በተለያዩ ቀበሌዎች ውስጥ የሚገኙ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

በአረርቲ ከተማ የሚገኙ ተፈናቃዮች የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ ጊዜውን ጠብቆ የሚቀርብ አለመሆኑን፣ የህክምና አገልግሎት አለመኖሩን፣ የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ አቅርቦት አለመኖሩን፣ ለህጻናት፤ ለነፍሰጡር ሴቶች እና ለአካል ጉዳተኞች የተለየ ድጋፍ የማይደረግ መሆኑን እና የንጹህ ውሃ አቅርቦት እጥረት መኖሩን፣ በተጨማሪም የመጸዳጃ ቤት ችግር ያለ መሆኑን፣ ነገር ግን ተፈናቃዮች በራሳቸው ገንዘብ ቤት ተከራይተው ለመኖር ቢሞክሩም የቤት ኪራይ ከፍያ በየግዜው የሚጨምር በመሆኑ ለከፍተኛ ችግር እየተዳረጉ መሆኑን፣ ለተማሪዎች ይቀርብ የነበረው የትምህርት ቁሳቁስ በመቋረጡ ምክንያት በርካታ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ማቋረጣቸውን እንዲሁም በመጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ የሚገኙ ተፈናቃዮች የሚያድሩበት ክፍል ጠባብ በመሆኑ ተጨናንቀው እና ተጣበው እንደሚኖሩ፣ በመጠለያ ጣቢያው የጸጥታና የሰላም ሁኔታን የሚቆጣጠር አካል የሌለ ቢሆንም አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በሀገር ሽማግሌዎች የሚፈታ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፣በተጨማሪም ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያው ከገቡ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደመጡበት ለመመለስ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል

4.18. ወርቄ መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣቢያ በሰሜን ወሎ ዞን ራያ ቆቦ ወረዳ ወርቄ ተብሎ በሚጠራ ገጠራማ አካባቢ የሚገኝ ሲሆን 20 ሴት፣50 ወንድ እና 70 ህጻናት በአጠቃላይ 140 ተፈናቃዮችን የያዘ በአንድ ክፍል ውስጥ በአማካኝ ከ10-20 ተፈናቃዮች የሚይዝ በቆርቆሮ የተሰሩ ከ15 በላይ ክፍሎች አሉት፡ ፡ በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች ከሃገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ማለትም ከኦሮሚያ ክልል ወለጋ ዞኖች እና ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከልና ካማሽ ዞኖች በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ናቸው፡፡ ይህ መጠለያ ጣቢያ ለአካባቢው ማህበረሰብ ተብሎ በመንግስት የተሰራ ሲሆን ተፈናቃዮች የራያ ቆቦ አቧሬ መጠለያ ጣቢያ በመጨናነቁ እና ተፈናቃዮች የነዋሪነት መታወቂያ ለማውጣት የተወለዳችሁበት አካባቢ መሄድ አለባችሁ በመባላቸው ወደዚህ መጠለያ ጣቢያ ሊገቡ ችለዋል፡፡

በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ ምንም አይነት የጤና ተቋም የሌለ ሲሆን ተፈናቃዮች በጤና መድህን ለመታከም ወደ መንግስት ጤና ጣቢያ በሚሄዱበት ወቅት እንደሚከለከሉና ለአላስፈላጊ ወጭዎች እየተዳረጉ መሆኑን፣ ፍራሽ፣ብርድልብስ እንደገብ የጠሰጣቸው ቢሆንም እረጅም ጊዜ የሆነው በመሆኑ ያረጀ አንዳንዱም አገልግሌት የማይሰጥ መሆኑን፣የምግብ አቅርቦት ወቅቱን ጠብቆ እንደማይመጣና ጥረቱን የጠበቀ አለመሆኑን፣ ትምህርትን በተመለከተ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ቢኖርም ለልጆች ምንም አይነት የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ ስለማይደረግላቸው

በአቅም እጥረት ምክንያት ልጆቻቸውን ከፍለው ማስተማር ባለመቻላቸው ትምህርት ማቋረጣቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ዘለቂ መፍትሄን እና ወደ ነበሩበት ቀያቸዉ የመመለስ ስራን በተመለከተ ቀደም ብለው የተሞከሩ ነገሮች ቢኖሩም በቂ እና የሰላሙ ሁኔታ አስተማማኝ ባለመሆኑ ተፈናቃዮች ለመመለስ ፈቃደኛ አለመሆናቸዉን፣ ተፈናቃዮች ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ያላቸዉ መስተጋብር አዎንታዊ ቢሆንም ነገር ግን አልፎ አልፎ መድሎና መገለል ሁኔታዎች የሚያጋጥማቸው መሆኑን፣ መጠለያ ጣቢያው ለአካል ጉዳተኞች፣ ለህፃናት እና ለአርጋዊያን የተለየ ድጋፍ አለመኖሩን፣በመጠለያ ጣቢያው የጸጥታና የሰላም ሁኔታን የሚቆጣጠር አካል የሌለ ቢሆንም አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በህገር ሽማግሌዎች የሚፈታ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፣ እንዲሁም ይህ መጠለያ ለአካባቢው ነዋሪዎች ለቀበሌ ቤት ተብሎ የተሰራ እንጅ ለእናንተ አይደለም በሚል ከመንግስት አካላት በኩል ለቃችሁ ውጡ እየተባሉ እንደሆነና ለከፍተኛ የስነልቦና ጫና ተጋላጭ መሆናቸውን ለኢሰመጉ ገልፀውለታል።

4.19. ጊራና መጠለያ ጣቢያ

ይህ መጠለያ ጣህቢያ በሰሜን ወሎ ዞን ሃብሩ ወረዳ የሚገኝ ሲሆን በውስጡ 152 ሴት፣124 ወንድ እና 124 ህጻናት በአጠቃላይ 400 ተፈናቃዮች ይገኛሉ። በዚህ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች ከ 2010 ዓ/ም ጀምሮ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተለይም ከኦሮምያ ክልል የወለጋ ዞኖች በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ሲሆን መጠለያ ጣቢያው የቆየና ከዚህ በፊት ለጤና ጣቢያ አገልግሎት ይሰጥ የነበረ ነው። የመጠለያ ጣቢያው እርቀት ያለው በመሆኑ ተፈናቃዮች እርዳታቸውን ለመቀበል ወደ ወረዳው ረጅም ርቀት በሚጓዙበት ጊዜ ለተለያዩ ተፈጥሯዊ አደጋዎች ማለትም ለደራሽ ወንዝ አደጋ እየተጋለጡ መሆኑን፣ መጠለያ ጣቢያው ያለበት አካባቢ ከፍተኛ ሙቀትና ቆላማ በመሆኑ ተፈናቃዮች ለወባ በሽታና ለተለያዩ አይነት በሽታዎች ተጋላጭ መሆናቸውን እና ይህንንም አስመልክቶ መንግስት ምንም አይነት ትኩረት ባለማድረጉና በአካባቢው የጤና አገልግሎት ባለመኖሩ ለህክምና ለአላስፈላጊ ወጭ እያወጡ መሆኑን እንዲሁም ለህክምና የሚከፍሉት በማጣታቸው ለከፍተኛ የጤና እክል ተጋላጭ መሆናቸውን ኢሰመጉ ለማወቅ ችሏል።

ለተፈናቃዮች የምግብ አቅርቦት ጊዜውን የጠበቀ አለመሆኑንና በአንድ ቤተሰብ 15 ኪሎ በቆሎና አንድ(1) ጣሳ ምስር የሚቀርብላቸው ቢሆንም በቂ አለመሆኑን፣ የትምህርት አገልግሎትን በተመለከተ ለህጻናት መደበኛ ትምህርት ባለመኖሩ ወላጆች በራሳቸው ወጭ ለማስተማር ባለመቻላቸው ህፃናት ከትምርት ገበታቸው እያቋረጡ መሆኑን እና የፍራሽ፣ብርድ ልብስ እና አንሶላ ወደ መጠለያው በገቡ ወቅት ተሰጥቷቸው የነበረ ቢሆንም ከዛ በኋላ ተሰጥቷቸው አለማወቁን፣ በመጠለያ ጣቢያው የጸጥታን ሁኔታ የሚቆጣጠር አካል ባለመኖሩ ተፈናቃዮች የጸጥታ ስጋት ያለባቸው መሆኑን እና ዘላቂ መፍትሄን በተመለከተ ወደነበሩበት ቦታ ለመመለስም ሆነ በቋሚነት ለማቋቋም የሚደረግ እንቅስቃሴ አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል።

5. አፋር ክልል

ኢሰመጉ በአፋር ክልል በተለያዩ ዞኖች ወረዳዎች እና ቀበሌዎች የሚገኙ ተፈናቃዮችን ከሐምሌ 8 -15 / 2017 ዓ.ም. ጉብኝት ያደረገ ሲሆን በመሬት መንቀጥቀጥ፣በጎርፍ እና በግጭት ምክንያት መፈናቀላቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በግጭት ምክንያት ከመኖሪያ አካባቢያቸው የተፈናቀሉት ኪቢላቲ ዞን መጋሌ 10,780 ፣ በረሃሌ ወረዳ 666፣ ማሒራሱ ያንግዲ ወረዳ 10,947፣ማሒራሱ ሲቢያቢ ወረዳ 13,480፣ ማሒራሱ-አዳ-አዶ ወረዳ 8,240፣ ጋቢራሱ ገዋኔ ወረዳ 7,084፣ ጋቢራሱ ጋላ ወረዳ 6,304፣ጋቢራሱ ሃናሩክ ወረዳ 17,472 በአጠቃላይ 74,973 ተፈናቃዮች በነዚህ ወረዳዎች የሚገኙ ሲሆን ጋቢራሱ ዞን በአዋሽ ፈንታሌ ወረዳ 37,122 እና ዱለሳ ወረዳ 22,914 ሰዎች በመሬት መንቀጥቀጥ ምክንያት የተፈናቀሉ መሆናቸውን እንዲሁም ጎርፍ ምክንያት የተፈናቀሉ ወደ 4,401 የሚጠጉ በአውሲራሱ አፋምቦ ወረዳ ተጠልለው የሚገኙ መሆኑን እና በአፋር ክልል 139,410 ተፈናቃዮች መኖራቸውን አፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የአደጋ መከላከል፣ ምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ኮሚሽን ለኢሰመጉ በሰጠው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

5.1. ገለአሌ፣ኡርዳ፣አሳይታ፣ሳህሌ፣አፋምቦ መጠለያ ጣቢያዎች

በእነዚህ መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ የሚገኙ ተፈናቃዮች ብዛት በአጠቃላይ 139,410 ሲሆን ተፈናቃዮች ለዘመናት ከብት አርብተው ኑሮአቸውን ከሚመሩበት የትውልድ መንደራቸው በመሬት መንቀጥቀጥ፣ ጎርፍ እና በግጭት ምክንያት ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ የተፈናቀሉ ተፈናቃዮች ናቸው፡፡ በእነዚህ መጠለያ ጣቢያዎች የሚቀርበው የምግብ አቅርቦት ለብዙ አመታት መቋረጡን፣ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ አቅርቦት ከተቋረጠ ከአመት በላይ መሆኑን፣ ከፍተኛ የሆነ የመድሀኒት አቅርቦት እጥረት መኖር እንዲሁም ለህጻናት የተለየ የምግብ አቅርቦት አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ቅርብ ጊዜ ከመሬት መንቀጥቀጥ ጋር በተያያዘ የተፈናቀሉት ተፈናቃዮች የተለያየ እርዳት አቅርቦት ያለ ሲሆን ነገር ግን ከነዚህ ውጭ ያሉት ተፈናቃዮች እርዳታ ጊዜውን ጠብቆ እንደማይቀርብላቸው፣ በመሆኑ ተፈናቃዮች ከፍተኛ ችግር ውስጥ መሆናቸውን እና በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት የተፈናቀሉት አብዛኞቹ ወደ ቀደመው መኖሪያ ቦታቸው የተመለሱ ሲሆን በረሃሌ እና መጋሌ ተብለው በሚጠሩ መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ የሚኖሩ ተፈናቃዮች ወደ ቀድሞው ቦታቸው ለመመለስ የፀጥታ ስጋት ስላለባቸው አሁንም በመጠለያ ጣቢያ ውስጥ ያሉ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከአሳይታ፣ ከሳህሌ፣ ከባርጌ፣ ከገለአሌ እና አፋምቦ አካባቢዎች የተፈናቀሉት በ2007 ዓ.ም. በመንግስት የተገነባው የተንዳሆ የመንግስት እርሻ ልማት ግድብ ላይ ተከትሮ የነበረው ውሃ ግድቡን ጥሶ የግጦሽ እና የእርሻ መሬታቸውን እንዲሁም የመኖሪያ ቤታቸውን በማጥለቅለቁና ብዙ ንብረታቸው ላይ ጉዳት በማድረሱ ምክንያት የተፈናቀሉ ሲሆን አካባቢው አሁን ድረስ

በውሃ ተሸፍኖ ያለ በመሆኑ ወደነበሩበት አካባቢም መመለስ አለመቻላቸውን ለማወቅ ተችሏል፡ ፡ ኢሰመጉ ጉብኝት ባደረገበት ወቅት ተፈናቃዮቹ በሱልጣን አሊሚራህ ጎሳ መሬት ላይ ቤት ሰርተው እየኖሩ ቢሆንም የሱልጣን አሊሚራ የጎሳ አባላት የእርሻ ወራት ሲደርስ ተፈናቃዮችን ለመልሶ መፈናቀል እንደሚዳረጉና የእርሻ ግዜ ሲደርስ ወደ አሳኢታ እና ሌላ ከተማ በመሄድ እርዳታ እንደሚጠይቁ መንግስትም ሆነ በግብረሰናይ ድረጅቶች የተሰራ መጠለያ ጣቢያ አለመኖሩን፣ ከዚህ ጋር ተያይዞም በመንግስትም ሆነ በግብረሰናይ ድርጅቶች የሚደረግ ምንም አይነት እርዳታ አለመኖሩን፣ እርዳታም የሚያገኙት በሴፍትኔት ከታቀፉ በኋላ ነው እንጅ በተፈናቃያ ነታቸው የሚያገኙት ልዩ ድጋፍ እንደሊለ እና በሴፍትኔት በወር ለአንድ ቤተሰብ 800 ብር ከመንግስት ይሰጣቸው የነበረ ቢሆንም የገንዘብ አርዳታው ከተቋረጠ አንድ አመት ያለፈው መሆኑን እና ለተማሪዎች ይቀርብ የነበረው የትምህርት ቁሳቁስ በመቋረጡ ምክንያት ህጻናት ትምህርት እያገኙ አለመሆኑን፣በተጨማሪም ተፈናቃዮች ከተፈናቀሉ እረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ወደመጡበት ለመመለስ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን እንዲሁም የተወሰኑት ተፈናቃዮች በአካባቢው ካለው የልማት እንቅስቃሴ ጋር በተገናኘ ከመኖሪያ ቦታቸው እንዲነሱ የተደረገ ቢሆንም ምትክ ቦታ ለመስጠትም ሆነ መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው አነስተኛ መሆኑን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለማወቅ ችሏል፡፡

በተጨማሪም ኢሰመጉ በ2007ዓ.ም ባወጣው 138ኛ ልዩ መግለጫ በአሳይታ እና አፋምቦ ወረዳዎች የሚገኙ ነዋሪዎች ለልማት ይፈለጋል ተብሎ በተለያዩ አካባቢዎች መሬታቸውን እዲለቁ በመደረጉ በከፍተኛ ችግር ውስጥ እንደሚገኙና ይህም የሆነው የተንዳሆ ስኳር ኮርፖሬሽን ፕሮጀክት ለማስፋፋት በማሰብ ነዋሪዎቹ ያፈሯቸውን የቴምር ዛፎች ያለምንም ካሳና ቅድመ ማስጠንቀቂያ በመቁረጥና ወደቴምር እርሻው ይፈስ የነበረውን የአዋሽ ወንዝ በመገደብ እና በማስፋፋት ወደ አፋምቦና አሳይታ እንዲፈስ በማድረግ መሆኑን በመግለጽ ንብረታቸውን አጥተው ለተፈናቀሉ ዜጎች ተለዋጭ ቦታ እና ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ መንግስት እንዲያመቻች በመግለጫው ተካቷል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ተፈናቃዮች መፍትሄ ሳያገኙ ለረጅም አመታት በመጠለያ ጣቢያ ውስጥ መሆናቸውን ለመረዳት የሚቻል ነው፡፡

6. የህግ ትንተና እና ግዴታዎች

የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን በተመለከተ ያሉ ህጎች እና የተጣሱ መብቶች የሰው ልጅ በተለያየ ምክንያት በአንድ ሀገር ውስጥ ሊፈናቀል ይችላል፤ ይኸውም በተፈጥሮ በሚከሰት አደጋ፣ በልማት ምክንያት እንዲሁም በግጭት ሲሆን፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ከስደተኞች በዋነኝነት የሚለያቸው መገለጫ የአንድን ሀገር የግዛት (የአስተዳደር) ወሰን አቋርጠው አለመውጣታቸው ነው። በሀገራችን በጉልህ የሚታየው እንዲሁም ይህ ልዩ መገለጫ በዋናነት ትኩረት የሚያደርገው እና ከዚህ በመቀጠል በስፋት በህግ ትንታኔው የሚዳሰሰው በግጭት ምክንያት የሚፈጠር መፈናቀልን ነው።

6.1. የካምፓላ ስምምነት እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የመመሪያ መርህ በሀገር ውስጥ መፈናቀል (United Nations General Principles on Internal Displacement)

የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን በተመለከተ ሀገራችን ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀችው የካምፓላው ስምምነት የውስጥ መፈናቀልን ለመከላከል፣ በሚፈናቀሉበት ወቅት ሰዎችን ለመጠበቅ እና ለመርዳት እንዲሁም ለተፈናቀሉ ሰዎች ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት የወጣ ህግ ሲሆን መንግስታትም እነዚህን ህጎች የማክበር፣ የማስከበርና በእነዚህ ህጎች ውስጥ የተጠቀሱ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን መብቶች የማሟላት ኃላፊነት እንዳለባቸው ተጠቅሷል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሀገር ውስጥ መፈናቀልን በሚመለከት ያወጣው የመመሪያ መርህ ሌላው ይህ ልዩ መገለጫ የሚዳሰሰው የህግ ማዕቀፍ ሲሆን ይህ መመሪያ በFrancis M. Dengin እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1998 የተዘጋጀ ነው። ምንም እንኳን ይህ መመሪያ እንደ ካምፓላ ስምምነት ገዢ አለማቀፍ ስምምነት (binding treaty) ባይሆንም በአለማቀፍ ደረጃ እንደ ዋና የህግና የተግባር መመዘኛ (authoritative standard) ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን ፣ አብዛኛዎቹ ድንጋጌዎችም ገዢ ከሆኑ አለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች ላይ መሰረት ተደርገው የተቀረፁ በመሆኑ መንግስታት ሊከተሏቸው የሚገቡ የህግ ግዴታዎችን ያካተቱ ናቸው። ለመንግስታት ጠቃሚ የሆነ ልምድን የሚሰጥ ከተለያዩ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ህግጋቶችና ከዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግጋቶች ጋር ተማጅ የሆነ መመሪያ ነው፡

መንግስት የዜጎቹን ደህንነት የመጠበቅ፤ መብታቸውን የማክበርና፣ የማስከበር እንዲሁም ፍላጎታቸውን የማሟላት ዓለማቀፋዊ፤ አህጉራዊ እንዲሁም ህገ-መንግስታዊ ግዴታ አለበት። ስለሆነም መንግስት ዜጎች ከመፈናቀላቸው በፊት ባሉበት ቦታ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ማድረግ ከተፈጠሩም በኋላ ቀድሞ በመከላከል (በመፍታት) ዜጎቹን ከመፈናቀል በቅድሚያ የመከላከል ሃላፊነት አለበት። ይህም የግጭት መንስኤዎችን ማጥናትና መፍታት፤ የማህበረሰብ ውጥረቶችን

ማርገብና አስቀድሞ የሚታዩ ምልክቶችን (early warning signs) መሰረት ያደረገ የመከላከል እርምጃ መውሰድን ይጨምራል።

የካምፓላ ስምምነት በአንቀጽ 2 (d) የስምምነቱን አላማ ሲዘረዝር ለስምምነቱ አባል ሀገራት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን በሚመለከት ከመፈናቀል ስለመጠበቅ፣ ከተፈናቀሉም በኋላ ጥበቃ ስለማድረግ እና ሰብአዊ ድጋፍ መስጠትን በተመለከተ ያለባቸውን ሃለፊነት እና ግዴታ ማሳወቅ እንደሆነ ይደነግጋል።" በተመሳሳይ የሀገር ውስጥ መፈናቀልን ስለመከላከል ስምምነቱ በአንቀጽ 3 ንኡስ አንቀጽ 1(a) ላይ የስምምነቱ አባል ሀገራት የሀገር ውስጥ መፈናቀልን መከላከል እንዳለባቸው ይደነግጋል። በተጨማሪም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሀገር ውስጥ መፈናቀልን በሚመለከት ያወጣው የመመሪያ መርህ በመርህ 6(1) ላይ ማንኛውም ሰው ከመኖሪያ ቦታው በዘፈቀደ ያለመፈናቀል መብት እንዳለው ይደነግጋል። ስለዚህ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለው መንግስት ዜጎችን የሀገር ውስጥ መፈናቀልን ሊያስከትሉ ከሚችሉ ነገሮች መከላከል እንዳለበት መረዳት እንችላለን። በዚህም መሰረት በተዘዋዋሪ ዜጎች ከሀገር ውስጥ መፈናቀል የመጠበቅ መብት አላቸው ብለን መደምደም ይቻላል።

የካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 3(1)(b) በግልጽ እንደተደነገገው በማህበራዊ ማንነታቸው፤ በሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ አመለካከታቸው የሰዎችን ወይም የማህበረሰቦችን መፈናቀል ሊያስከትሉ ከሚችሉ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ መገለልን እና ፍረጃ መከላከል የሚል ሲሆን ይህ መርህ በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልል ውስጥ በህግ የተደነገገውን የመድልኦ ስርዓት በቀጥታ ይሞግታል። የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 2 በርታ፣ ጉሙዝ፣ ሽናሻ፣ ማኦ እና ኮሞ የተባሉትን አምስት ብሔረሰቦች የክልሉ 'ባለቤቶች' በማለት በህግ ይደነግጋል። ይህ ድንጋጌ በወረቀት ላይ ብቻ የቀረ አይደለም፤ 'ባለቤት' እና 'ሌላ' በሚል የፈጠረው ህጋዊ ተዋረድ በተግባርም ይገለጻል። 'ባለቤት' ተብለው ያልተጠቀሱት ሌሎች ብሔሮች በተለይም የአማራ ተወላጆች፣ በመሬት ይዞታ ማረጋገጫ፣ በአካባቢ አስተዳደር ተሳትፎ፣ እና በጸጥታ ከለላ የማግኘት መብታቸው ላይ በተጨባጭ መድልኦ እንደሚደርስባቸው በርካታ መረጃዎች ያሳያሉ። ይህ በህግ የተደገፈ መድልኦ (de jure discrimination) 'መጤ' ወይም 'ሰፋሪ' ተብለው ለሚፈረጁት ዜጎች የሁለተኛ ዜግነት ስሜት ከመፍጠሩም በላይ፣ በእነሱ ላይ ለሚፈጸም ጥቃት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በመሆኑም፣ በክልሉ የተፈጸመው የኃይል እርምጃና የግዳጅ ማፈናቀል ድንገተኛ ክስተት ሳይሆን፣ መንግስት በህግ አውጥቶ በፈጠረውና ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ አስቀድሞ መገመት በነበረበት (foreseeable consequences) መድልኦ የተቀሰቀሰ ነው።

በተጨማሪም በካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 4(1) አባል ሀገራት ለሀገር ውስጥ መፈናቀል ምክንያት የሚሆኑ ነገሮችን ለመከላከል እና ለማስቆም ይረዳ ዘንድ በዓለም አቀፍ ህጎች በሰብዓዊ መብቶች እና በሰብዓዊነት ህጎች ላይ የተቀመጡ ግዴታዎቻቸውን ማክበር እንዳለባቸው ይደነግጋል።

ይኸው አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 4(d) ላይ ሁሉም ሰው በተጠቃለለ ጥቃት ወይም በሰብዓዊ መብት ጥሰት ምክንያት ከሚደርስ መፈናቀል የመጠበቅ መብት አለው ሲል ዜጎች ከመፈናቀል የመጠበቅ መብት እንዳላቸው ደንግጓል፡፡ ነገር ግን በሀገራችን ኢትዮጵያ ያለውን ሁኔታ ስንመለከት በዋናነት ከላይ የተመለከትናቸው ኢሰመጉ በክትትል ስራ የሸፈናቸውን አካባቢዎች ማለትም፣ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል ፣ በኦሮሚያ ክልል ፣ በአማራ ክልል እና በአፋር ክልል የተለያዩ አካባቢዎች የደረሱ መፈናቅሎችን ስንመለከት ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች ላይ ጥሰት እንደተፈፀመ እና መንግስት ዜጎችን ከሀገር ውስጥ መፈናቀል ለመከላከል ያለበትን ሃላፊነት እንዳልተወጣ መረዳት ይቻላል፡፡

የካምፓላ ስምምነት እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሀገር ውስጥ መፈናቀልን በሚመለከት ያወጣው የመመሪያ መርህ የስምምነቱ አባል ሀገራት ዜጎችን ከሀገር ውስጥ መፈናቀል መጠበቅ እንዳለባቸው የሚደነግጉ ቢሆንም ይህ ሳይሆን ቀርቶ የዜጎች መፈናቀል በተለያዩ ምክንያቶች (በልማት፣ በተፈጥሮ አደጋ እና በግጭት) ቢከሰት ስምምነቱ በአባል ሀገራት ላይ ተጨማሪ ግዴታዎችን የሚጥል ሲሆን እነዚህ ግዴታዎችም በመመሪያው ላይ በግልጽ ተቀምጠው ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ግዴታዎች መካከል የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ደህንነት መጠበቅ እና ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሰብዓዊ ድጋፍ ማድረግ ይገኙበታል፡፡ ነገር ግን መንግስት ይህን ግዴታውን ለመወጣት ተገቢውን ትጋት (Due-diligience) ለተፈናቃዮች የሰብዓዊ ድጋፍ ማድረግ ባለበት መጠን ድጋፍ እያደረገ አለመሆኑን ኢሰመጉ ባደረገው ክትትል ለማወቅ ችሏል፡፡

ስምምነቱ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ አባል ሀገራት በድንበሮቻቸው ውስጥ ለሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሰብአዊ ድጋፍ እና ጥበቃ ያለምንም አድልዎ በማቅረብ ረገድ ተቀዳሚ ሀላፊነት እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሀገር ውስጥ መፈናቀልን በሚመለከት ያወጣው የመመሪያ መርህ በመርህ 3(፩) ላይ ከካምፓላ ስምምነት ጋር ተመሳሳይ በሚባል ደረጃ መንግስታት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የመጠበቅ እና ድጋፍ የማድረግ ተቀዳሚ ሀላፊነት እንዳለባቸው በግልጽ አስቀምጧል፡፡ ከነዚህ ድንጋጌዎች የምንረዳው በቀዳሚነት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን መርዳት እና ጥበቃ የማድረግ ሃላፊነት የሀገሪቱ መንግስት መሆኑን ነው፡፡

ከካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2(b) እና (c) የጋራ ንባብ እንደምንረዳው መንግስት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በተቻለ መጠን ሳይዘገይ በቂ ሰብዓዊ ድጋፍ ምግብ፣ ውሀ፣ መጠለያ፣ የህክምና እንክብካቤ እና ሌሎች የጤና አገልግሎቶች፣ የንጽህና አጠባበቅ፣ ትምህርት እና የትኛውንም አይነት አስፈላጊ ማህበራዊ አገልግሎት እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይህንን ድጋፍ ለተቀባይ ማህበረሰብ ማድረግ እንዳለበት፤ ልዩ ጥበቃ እና ሰብዓዊ ድጋፍ ካሉበት ሁኔታ አንጻር ልዩ ድጋፍ ለሚሹ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ማለትም ከቤተሰቦቻቸው ለተለዩ ህጻናት፣ ለእማወራዎች፣ ለነፍሰጡር ሴቶች፣ ህጻናት ልጆች ላሏቸው ሴቶች፣ ለአዛውንቶች፣

ለአካል ጉዳተኞች እና ለተላላፊ በሽታ ታማሚዎች መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በተመሳሳይ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሀገር ውስጥ መፈናቀልን በሚመለከት ያወጣው የመመሪያ መርህ በመርህ 18 እና 19 ላይ እያንዳንዱ የሀገር ውስጥ ተፈናቃይ በቂ የኑሮ ደረጃ የማግኘት መብት እንዳለው፣ መንግስትም በምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ ቢሆንም ያለ ምንም አድልዎ ቢያንስ አስፈላጊ ምግብ እና ንጹህ ውሀ፣ መጠለያ፣ ልብስና አስፈላጊ የህክምና እና የንጽህና አገልግሎት ማቅረብ እንዳለበት እንዲሁም ድጋፍ በሚሰጥበት ሰዓት ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ የህበረተሰብ ክፍሎችንም ጨምሮ ይዟል፡፡ በተጨማሪም ይኸው የመመሪያ መርህ ትምህርትን በሚመለከት በመርህ 23 ላይ ሁሉም ሰው የመማር መብት እንዳለው በመግለጽ ይህ መብት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችም የተሰጠ መሆኑን እና መንግስትም ይህንን መብት በዋናነት ለተፈናቀሉ ህጻናት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በነጻና በአስገዳጅ መልኩ ማቅረብ እንዳለበት እንዲሁም ይህ ትምህርት ባህላዊ ማንነታቸውን፣ ቋንቋቸውን እና ሀይማኖታቸውን ማከበር እንዳለበት አስቀምጧል፡፡

የካምፓላ ስምምነት እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሀገር ውስጥ መፈናቀልን በሚመለከት ያወጣው የመመሪያ መርህ ይህንን ይበሉ እንጂ በሀገራችን ያለውን እውነታ ስንመለከት ከላይ በተጠቀሱት ከልሎች የተፈናቀሉት ሰዎች የትምህርት፤ የህክምና አገልግሎት እና የንጽህና መጠበቂያ እያገኙ አይደለም ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ ላይ ይገኛሉ፡፡

በሀገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች የመማር መብት እንዳላቸው የሚደነግግ ቢሆንም በአብዛኛው ማለት በሚያስችል ደረጃ፣ ህጻናት ትምህርት እያገኙ አይደሉም፡፡

የካምፓላ ስምምነት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የተለያዩ መብቶችን እንዲሁም ለአባል ሀገራት የተለያዩ ግዴታዎችን አካቷል፡፡ ከግዴታዎቹ መካከል የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ደህንነት ማስጠበቅ ይገኝበታል፡፡ ስምምነቱ በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1(d) ላይ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በየትኛውም ምክንያት የተፈናቀሉ ቢሆንም ከሚደርስባቸው ማንኛውም አይነት ጾታዊ ጥቃት በተለይም አስገድዶ መድፈር፣ የግዳጅ፣ ወሲባዊ ብዝበዛ እና ጎጂ ልማድ፣ ባርነት፣ ህጻናትን ለግጭት መመልመል እና መጠቀም፣ የግዳጅ የጉልበት ስራ፣ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር እና ንግድ የመጠበቅ መብት እንዳላቸው ይገልጻል፡፡

የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በተለይም ሴቶች እና ህጻናት በከፍተኛ ሁኔታ ለጉዳት እና ለተለያዩ የሰብዓዊ መብቶ ጥሰቶች ተጋላጮች በመሆናቸው መንግስት በአጠቃላይ የሀገረ ውስጥ ተፈናቃዮችን፣ በዋናነት ደግሞ እነዚህን ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ከመሰል ጥቃቶች መከላከል እንዳለበት ከዚህ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡

በካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 2 (k) እና በአንቀጽ 11 ንኡስ አንቀጽ (2) ላይ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች በጋራ በምንመለከትበት ሰዓት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ደህንነት እና ድጋፍ በሚመለከት በሚወሰኑ ውሳኔዎች ላይ የስምምነቱ አባል ሀገራት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ማማከር እና ውሳኔዎች ላይ ተሳታፊ ማድረግ እንዳለባቸው፤ የስምምነቱ አባል ሀገራት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ወደመጡበት አካባቢ ለመመለስ፣ ተፈናቅለው ባሉበት አካባቢ ለማስፈር ወይም ወደሌላ ቦታ ማዘዋወርን እንዲሁም ሌሎች አማራጮችን በሚመለከት የሀገር ውስጥ ተፈናቃች ነጻ ምርጫ እንዲመርጡ ማስቻል እና ዘላቂ መፍትሄ በማበጀቱ ረገድ ተሳትፏቸውን ማረጋገጥ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ ይህም ማለት ተፈናቃዮች ህይወታቸውን በሚመለከቱ ውሳኔዎች ላይ የመረጃ ተቀባይ ብቻ ሳይሆኑ ፣ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ ውስጥ ንቁ ተሳታፊዎች ሊሆኑ ይገባል። ያለነሱ ሙሉ ተሳትፎና ፈቃድ የሚወሰን «መፍትሄ» ዘላቂ ሊሆን አይችልም።

በተጨማሪም የካምፓላ ስምምነት በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 (e) ላይ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በሌላ የሀገሪቱ አካባቢ ደህንነት የማግኘት እና ህይወታቸውን፣ ደህንነታቸውን፣ ነጻነታቸውን እና ጤንነታቸውን አደጋ ላይ ወደሚጥል ወደመጡበት አካባቢ በግዴታ ከመመለስ ወይም ወደ ሌላ ቦታ ከመዘዋወር የመጠበቅ መብታቸውን አባል ሀገራት የማክበር እና የማረጋገጥ ሀላፊነት እንዳለባቸው በግልጽ አስቀምጧል፡፡ በተመሳሳይ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሀገር ውስጥ መፈናቀልን በሚመለከት የወጣው የመመሪያ መርህ በመርህ 15 ላይ በግዴታ ወደ መጡበት አካባቢ ከመመለስ ወይም ደህንነታቸውን፣ ህይወታቸውን፣ ነጻነታቸው እና ጤናቸውን አደጋ ላይ ወደሚጥል ወደሌላ አካባቢ በግዴታ ከመዘዋወር የመጠበቅ መብት አላቸው ሲል ይደነግጋል፡ ፡ ለማሳያ ያህልም በደቡብ ወሎ ዞን ደሴ ዙሪያ ወረዳ በገራዶ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ከኦሮምያ ክልል ምስራቅ ወለጋ ዞኖች የተለያዩ አካባቢዎች ተፈናቅለው የሚገኙ ተፈናቃዮች የፀጥታ ሁኔታ ባልተሻሻለበት ሁኔታ እና በጥናት የታገዘ የአካባቢውን ሁኔታ ግምት ውስጥ ባላስገባ ሁኔታ ወደቀያቸው እንዲመለሱ የተነገራቸው ቢሆንም ነገር ግን ተፈናቃዮች በራሳቸው በአካባቢው ያለውን የጸጥታ ሁኔታ ያልተስተካከለ በመሆኑ መመለስ እንደማይችሉ የገለጹ ቢሆንም የመንግስት አካላት ግን ወደመጡበት አካባቢ እንዲመለሱ ጫና እያደረጉ መሆኑን ኢሰመጉ ለማወቅ ችሏል፡፡

የካምፓላ ስምምነት በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የስምምነቱ አባል ሀገራት በአባል ሀገር ጥያቄ መሰረት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ድጋፍ እና ጥበቃ በማድረጉ ላይ መደጋገፍ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ይኸው ስምምነት በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 6 ላይ አባል ሀገራት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በቂ የሆነ ድጋፍ እና ጥበቃ ማድረግ እንዳለባቸው፤ ይህንን ድጋፍ እና ጥበቃ ለማድረግ ያሉ ግብአቶች በቂ ሳይሆኑ ሲቀሩ የዓለም አቀፍ ድርጅቶችን እና ሰብዓዊ ተቋማትን፣ ሲቪክ ማህበራትን እና ሌሎች ተዋናዮችን ማፈላለግ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡

በተጨማሪም የካምፓላ ስምምነት በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ አባል ሀገራት በዓለም አቀፍ ህግ መሰረት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የአፍሪካ ህብረትን እና የተባበሩት መንግስታትን ሀላፊነት እንዲሁም የዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ ድርጅቶችን ጥበቃ እና ድጋፍ የማድረግ ሀላፊነት እንዲያከብሩ ይደነግጋል፡፡

ስለሆነም ከላይ ከተዘረዘሩት የህግ ድንጋጌዎች መረዳት የምንችለው ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ድጋፍ እና ጥበቃ ማድረግ ተቀዳሚ ሃላፊነት የመንግስት ቢሆንም መንግስት የተባበሩት መንግስታትን፣ የአፍሪካ ህብረትን እንዲሁም ሰብዓዊ ድጋፍ የሚያደርጉ አለም አቀፍ ተቋማትን ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ድጋፍ የማድረግ ሀላፊነት ሊያከብር እንደሚገባ መረዳት ይቻላል፡ ፡ በተጨማሪም መንግስት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ድጋፍ እና ጥበቃ በሚያደርግበት ወቅት የግብዓት እጥረት ሲያጋጥም የእነዚህን ተቋማት ድጋፍ ማፈላለግ እንዳለበት መረዳት ይቻላል፡፡ በሀገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎችን ለመጠበቅ ድጋፍ የማድረግ የአፍሪካ ህብረት ስምምነት (የካምፓላ ስምምነት) ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 1187/2020 ላይ የኢትዮጵያ መንግስት የተለያዩ ተአቅቦዎችን እና መግለጫዎችን ያስቀመጠ ሲሆን ከነዚህም መካከል አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2(b) ላይ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፣ የአፍሪካ ህብረት እና ሌሎች ሰብዓዊ ድርጅቶች ለተፈናቃዮች ጥበቃ እና ድጋፍ መስጠት የሚችሉት መንግስት የቅድሚያ ፈቃድ ሲሰጥ ነው የሚለውን መግለጫ ያስገባል ሲል ጠቅሷል፡፡ ስለዚህ በዚህ መግለጫ መሰረት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፣ የአፍሪካ ህብረት እና ሌሎች የሰብዓዊ ድርጅቶች ለተፈናቃዮች እርዳታ ማድረግ የሚችሉት ከመንግስት ቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት ከቻሉ ብቻ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያ መንግስት ለተፈናቀሉ ሰዎች በተቻለው አቅም ለተፈናቀሉ ሰዎች እርዳታ ከማድረግ አልፎ ማንኛውም አይነት የቢሮክራሲያዊም ሆነ ሌሎች ማነቆዎችን በማንሳት ሌሎች የሰብዓዊ ድርጅቶች ለተቸገሩ ዜጎች ያለገደብ እርዳታ ማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታ ማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

6.2. በካምፓላ ስምምነት ላይ የተደረጉ ተአቅቦዎች እና መግለጫዎች

የኢትዮጵያ መንግስት በሃገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎችን ለመጠበቅ እና ድጋፍ የማድረግ የአፍሪካ ህብረት ስምምነትን (የካምፓላ ስምምነት) ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ.ም የፈረመች ሲሆን መጋቢት 4 ቀን 2012ዓ.ም በ አዋጅ ቁጥር 1187/2020 አጽድቃለች፡፡ ስምምነቱን ያጸደቀች ቢሆንም በተወሰኑ አንቀጾች ላይ ተዓቅቦዎችን (Reservation) እና መግለጫዎችን (Declaration) አድርጋለች፤ በስምምነቱ ላይ የገቡ መዓቅቦዎች አንቀጽ 12(2)(3) እና 22 እና መግለጫዎች አንቀጽ 1(ተ) እና 5(6)(7) መመልከት ይቻላል፡፡

ኢትዮጵያ ስምምነቱ ላይ ተአቅቦ ያደረገችበትን አግባብ ስንመለከት ፤ የካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 12(2) መንግስት በመፈናቀል ምክንያት ለደረሰባቸው ጉዳት ፍትሀዊና ሚዛናዊ ካሳ እና ሌሎች

ማሻሻያዎችን ለመስጠት የሚያስችል ውጤታማ የህግ ማዕቀፍ ማቋቋም አለበት የሚል ሲሆን፣ የኢትዮጵያ መንግስት እዚህ አንቀጽ ላይ ተአቅቦ አድርጓል፤ ይህም ካሳ የሚከፈለው ለህዝብ ጥቅም ተብሎ የግል ቦታ በመወሰዱ በሚደርስ መፈናቀል ወቅት ነው ነገር ግን በህገመንግስቱ አንቀጽ 89(3) መሰረት በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ መንስኤዎች ለሚደርስ መፈናቀል መንግስት ያለበት ሀላፊነት ድጋፍ ማድረግ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ እዚህ አንቀጽ ላይ ተአቅቦ ለማድረግ መሰረት ያደረገው ኢትዮጵያ ካላት ኢኮኖሚ አንጻር ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ካሳ የመስጠት አቅም ካለመኖር አንጻር የተደረገ ነው ለማለት የሚያስችል ነው፡፡

የስምምነቱ አንቀጽ12 (3) በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት መንግስት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ማድረግ ያለበትን ነገር ሳያደርግ ቢቀር ማለትም የተፈናቀሉ ዜጎችን ከመከላከልና ከመርዳት ሲቆጠብ ተጠያቂ እንደሚሆን ያስረዳል፤ ነገር ግን ኢትዮጵያ በዚህ አንቀጽ ላይ ያደረገችው ተአቅቦ በግለሰቦች ወይም በተቋማት ህግ በመጣሳቸው ምክንያት ተፈናቃዮች ድጋፍ ሳይደረግላቸው ቢቀር ጥፋተኞች ተጠያቂ እንዲሆኑና የድጋፍ አቅርቦቱ እንዲቀጥል የማድረግ ግዴታ እንዳለበት በሚል ትርጉም ተሰጥቶት እናያለን፤ ነገር ግን መንግስትስ ለተፈናቀሉ ዜጎች ድጋፍ ሳያደርግ ቢቀር ተጠያቂ ይሆናል ወይ? የሚለውን ጥያቄ ስናነሳ መልስ የሚሰጥ አይደለም፡፡ ይህም የመከላከልና ፈጣን ምላሽ የመስጠት ግዴታውን የሚያዳክም ከመሆኑም በላይ ፥ ተጠያቂነት የሌለበት ስርአት (system of impunity) በመፍጠር የተፈናቃዮችን መብት በእጅጉ ይጎዳል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሀገር ውስጥ መፈናቀልን በሚመለከት ያወጣው የመመሪያ መርህ በመርህ 29 ላይ ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ንብረታቸውን መመለስ ካልተቻለ በቂ ካሳ ሊሰጣቸው እንደሚገባ በግልጽ ተቀምጦ እናገኛለን፡፡

መንግስት በስምምነቱ መሰረት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የመርዳትና የመጠበቅ ሀላፊነት አለበት በሌላ መልኩ ስንመለከተው የካምፓላ ስምምነት ዋና አላማው የውስጥ መፈናቀልን ለመከላከል፣ በሚፈናቀሉበት ወቅት ሰዎችን ለመጠበቅ እና ለመርዳት እንዲሁም ለተፈናቀሉ ሰዎች ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት ነው፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ መንግስት ለተፈናቀሉ ሰዎች በተወሰነ ደረጃ ድጋፍ ከማድረጉ ውጪ ካሳ አይከፍልም፤ በተጨማሪም የተፈናቀሉ ሰዎች ወደ ነበሩበት የኑሮ ሁኔታ ለመመለስ በቂ ድጋፍ አያደርግም፤ ይህ ደግሞ ከካምፓላ ስምምነት አላማ ጋር የሚጋጭ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ተቀብላ ባጸደቀቻቸው አለም አቀፋዊና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች እንዲሁም የሀገሪቱ ህገ መንግስትም ላይ በግልጽ ተቀምጦ እንደምናየው ማንም ሰው ሰብአዊም ሆነ ዴሞክራሲያዊ መብቱ ተጠብቆለት የመኖር መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡

መንግስት ስምምነቶችን ተቀብሎ ከማጽደቅና የሀገሪቱ የህግ አካል ከማድረግ ውጪ ተግባራዊነቱ ላይ ሰፋ ያለ ክፍተት ይስተዋላል፡፡ ዜጎች ከቀያቸው እንዳይፈናቀሉ ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ፤ ከተፈናቀሉ በኋላ ጥበቃና ድጋፍ ማድረግ፤ ብሎም ወደነበሩበት የኑሮ ሁኔታ እንዲመለሱ የማድረግ ሃላፊነት ያለበት ቢሆንም ይህንን ሀላፊነት ወደጎን በመተው ዜጎች ሰብአዊ መብቶቻቸው ተጥሰው ለእንግልት ተዳርገዋል በሀገራችን ከጊዜ ወደጊዜ እየተበራከተ የመጣው የተፈናቃይ ቁጥር መንግስትን ሊያሳስበው የሚገባ ነገር ቢሆንም ለጉዳዩ በቂ ትኩረት ባለመስጠቱ ምክንያት ለሚደርስ የብዙ ንጹሀን ዜጎች መፈናቀልና እንግልት መንግስት ተጠያቂ ነው፡፡

7. ማጠቃለያ

ይህ 157ኛ ልዩ መግለጫ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብዓዊ መብት አያያዝ ሁኔታ ላይ የተዘጋጀ ሲሆን ይህ የክትትል ስራ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ አማራ፣ አፋር እና ኦሮምያ ክልሎች በሚገኙ 46 ተፈናቃዮችን ጣቢያ የክትትል ባልሞያዎችን በማሰማራት ተፈናቃዮችን በአካል በማግኘት ተፈናቃዮችን ቃለመጠይቅ በማድረግ ፣ በአካባቢው የሚገኙ የአደጋ ስጋት እና ቅድመ ማስጠንቀቂያ ቢሮ ሰራተኞችን ቃለ መጠይቅ በማድርግ እንዲሁም በአካል በመገኘት መጠለያ ጣቢያዎችን በመጎብኘት የተዘጋጀ ልዩ መግለጫ ነው፡፡ በዚህ ልዩ መግለጫም በዋናነት የሀገር ውሰጥ ተፈናቃዮች የተፈናቀሉት በአካባቢያቸው ባለ ግጨት የተነሳ መሆኑን፣ የምግብ አቅርቦት ጊዜውን ጠብቆ እንደማያቀርብ በአማካኝ በሶስት ወር ጊዜ የሚቀርብ መሆኑን እና የሚቀርበው የምግብ አቅርቦት በቂ እንዳልሆነ እና ጥራቱንም የጠበቀ አለመሆኑን፣ የሚኖሩበት መጠለያ ጣቢያ አብዛኛውን የተጨናነቀ እና ያረጁ መሆናቸውን፣ የሴቶች የንፅህና መጠበቂያ በአብዛኛው መጠለያ ጣቢያ አቅርቦት እንደሌለ በተወሰኑ መጠለያ ጣቢያዎች እንደተቋረጠ፣ ፍራሽ፣ ብርድ ልብስ፣ አንሶላ ከቀረበላቸው ረጅም ጊዜ የሆነው ቢሆንም ቅያሪ ቀርቦላቸው እንደማያውቅ የህክምና አቅርቦት በግብረ ሰናይ ድርጅቶች በተወሰኑ የመጠለያ ጣቢዎች ውስጥ የነበረ ቢሆንም ኢሰመጉ ጉብኝት ባደረገበት ጊዜ እየወጡ የነበሩ መሆኑን ለመገንዘብ ችሏል። በዚህም የተነሳ ለከፍተኛ ችግር የተዳረጉ መሆኑን አንዳንድ አካባቢ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ተቀላቅለው የህክምና አገልግሎት የሚያገኙ ቢሆንም የጤና መድህን እንዲያዋጡ እንደሚጠየቁ እና የሚከፈለውን ክፍያ መክፈል የማይችሉ ተፈነናቃዮች የህክምና አገልግሎት ማግኘት እንዳልቻሉ፣ የትምህርት አቅርቦት በአብዛኛው መጠለያ ጣቢያ እንደሌለና ከአከካባቢው ማህበረሰብ ጋር ተቀላቅሎ ለመማርም ብዙ ጊዜ መጠለያ ጣቢያው የሚገኝበት ቦታ ከከተማ ውጭ ስለሆነ እና የመመዝገቢያ ክፍያ የሚጠይቁ ትምህርት ቤቶችም ስላሉ እና መክፈል ስለማይችሉ ማስተማር እንዳልቻሉ፣ አብዛኛው መጠለያ ጣቢያ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋዊያን ምቹ አለመሆኑን፣ በአማካኝ ተፈናቃዮች ከተፈናቀሉ ሶስት ዓመት እና ከዛ በላይ የሆናቸው ቢሆንም ወደ መጡበት ለመመለስ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን ኢሰመጉ ካሰበባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡ መንግስት ከካምፓላው ስምምነት አኳያ የውስጥ መፈናቀልን መከላከል፣ በሚፈናቀሉበት ወቅት ሰዎችን መጠበቅ እና መርዳት እንዲሁም ለተፈናቀሉ ሰዎች ዘላቂ መፍትሄ መስጠት ያለበት መሆኑን የሚደነግግ ቢሆንም እና በዚህ ስምምነትና ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው ዓለማቀፋዊ ስምምኖች እንዲሁም በህገ-መንግስቱ የዜጎቹን ደህንነት የመጠበቅ፤ መብታቸውን የማክበርና፣ የማስከበር እንዲሁም ፍላጎታቸውን የማሟላት ግዴታ መንግስት ያለበት መሆኑ ተደንግጎ የሚገኝ ቢሆንም መንግስት እነዚህን ግዴታዎቹን በአግባቡ እየተወጣ አለመሆኑን ኢሰመጉ ለመገንዘብ የቻለ ሲሆን በአጠቃላይ በዚህ የክትትል ስራ መንግስት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መብት ለማስጠበቅ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራ የሚገባው መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎችን አሰባስቧል ::

ቁ	ክልል	መጠለያ ጣቢያ	ሴት	ወንድ	ህፃናት	ጠቅላላ(ድምር)	ምርመራ
ሀ.	**ቢኒሻንጉል**						የህፃናት ቁጥር የሚያሳይ ማስረጃስላልተገኘ አልተካተተም
1		ማንቡክ	2,354	1,982		4,336	
2		ግልገል በለስ 02 ቀበሌ /ቻይና ካምፕ	1,730	1781		3,511	
3		ግልገል በለስ 01 ቀበሌ	159	160		319	
4		ገነተ ማሪያም	2,550	2,476		5,026	
	ድምር		6,796	6,399		13,192	
ለ.	**ኦሮምያ**						በአንዳንድ ጣቢያዎች የህፃናት ቁጥር የሚያሳይ ማስረጃ ስላልተገኘ አልተካተተም
1		ደደር	2,795	2,195	1,764	6,754	
2		ቦርደዴ	797	621		1,418	
3		ጡሎ/ሂርና	162	127	28	378	
4		ጅማ	615	1,767	1,135	3,517	
5		ቲሬጉዶ/ጭናቅሰን	235	266		500	
6		ሙያዲን	654	280		934	
7		ባቢሌ	326	313		639	
8		አሞ ከተማ 01 ቀበሌ	2342	844	1524	4,710	
9		አርጆ ጉደቱ ከተማ 01 ቀበሌ	1123	1,047	1,756	3,926	
10		ገንዳ ለሚ	797	621		1,423	
11		ገንደ ድንቁ	239	187		429	
12		ሊጊዴ	223	237		460	
13		ቀርሳ ካምፕ	365	299	1584	2,255	
14		01 ቀበሌ የጎልማሶች ማህበር	2,466	2,282		4,748	
15		ግራዋ ወረዳ 02 ቀበሌ	93	120		213	
	ድምር		13,232	11,202	**7791**	32,229	
ሐ.	**አማራ**						በአንዳንድ ጣቢያዎች የህፃናት ቁጥር የሚያሳይ
1		መካነ እየሱስ	726	688	647	2,061	

2		ግብርና ግቢ	79	70		149	ማስረጃ ስላልተገኘ አልተካተተም
3		ላም እርባታ	51	47		91	
4		ቀበሮ ሜዳ	663	721	269	1,620	
5		ሺ-መላኩ	247	442		689	
6		ወይንሸት	5,969	5,634		11,603	
7		ቻይና ካምፕ	3,700	3,300		7,000	
8		ባቄሎ	836	501		1,337	
9		ገራዶ	302	232		534	
10		ቻይና ካምፕ/ደጋን	430	452	850	1,905	
11		መዳና	334	482		816	
12		ኮሌጅ	85	57		142	
13		አቧሬ	370	330		700	
14		መርሶ	170	194		364	
15		ጃራ	4,076	4,752	837	9,665	
16		ማይብሎት	28	29		57	
17		አበርገሌ	2,661	2,481		5,142	
18		ሸዋሮቢት	339	383		722	
19		አጣየ ከተማ	8,321	8,674		16,995	
20		ምንጃር ሸንኮር(አረርቲ፣ ልካጅሎ)	836	804		1,740	
21		ወርቄ	20	50	70	140	
22		ጊራና	152	124	124	400	
	ድምር		**30,395**	**30,447**	**2,797**	**63,639**	
መ.	**አፋር**						
1		ገለኢሎ				139,410	ይህ መረጃ የተገኘው ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ሲሆን፤ የእያንዳንዱን መጠለያ ጣቢያ ተፈናቃይ ቁጥር በየቃ፥ በህጻናት ቁጥርም ይሁን የተጠቃለለ መረጃ
2		ኡርዳ					
3		አሳይታ					
4		ሳህሌ					
5		አፋምቦ					

							ለማግኘት ኢሰመጉ ያደረገው ጥረት አልተሳካም። ይህ ቁጥር ከ1-5 በአፋር ክልል መጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙትን አጠቃላይ የተፈናቃዮች ቁጥር የሚወክል ነው።
	ድምር					139,410	
	ጠቃላይ ድምር					**248,470**	

8. ምክረ ሃሳብ

✓ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ተፈናቃዮች በመጠለያ ጣቢያ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የሚገኙ ሲሆን ይህ ደግሞ መንግስት ተፈናቃዮችን ወደመጡበት አካባቢ የመመለስ፣ ባሉበት አካባቢ የማቋቋም እና ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው እራሳቸውን እንዲችሉ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ቢሆንም ይህንን ባለመወጣቱ ተፈናቃዮች ለከፍተኛ የመብት ጥሰት እየተዳረጉ በመሆኑ መንግስት በካምፓላ ስምምነት ላይ የተገለጹ ኃላፊነቶቹን ይወጣ፣

✓ በመጠለያ ጣቢያ ውስጥ የሚገኙ ተፈናቃዮች ከራሳቸው አልፈው ሌሎችን መርዳት የሚያስችል አቅም ያላቸው እና መስራት የሚችሉ ቢሆንም ነገር ግን መጠለያ ጣቢያ ውስጥ ከገቡ ጀምሮ በራሳቸው መስራት የሚያስችል ሁኔታ ባለመኖሩ እርዳታ ጠባቂ ሆነዋል በመሆኑም መጠለያ ጣቢያዎች ያሉባቸው የከልል መንግስታት እና የቅድመ ማስጠንቀቂያ እና አደጋ መከላከል ቢሮዎች እነዚህ ሁኔታዎች እንዲስተካከሉ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉ፣

✓ መንግስት ተፈናቃዮችን ቀድሞ ወደነበሩበት ቦታ የሚመልስ ከሆነ የተፈናቃዮችን ፍላጎች እና ፈቃድ መሰረት ባደረገ መልኩ ውይይት በማድረግ እና የተፈናቀሉበትን አካባቢ ሰላማዊነቱን በማረጋገጥ ለኑሮ ምቹ እና ተገቢውን ጥበቃ በማድረግ ለዜጎቹ አስተማማኝ የሆነ መሆኑን በማረጋገጥ ሊሆን ይገባዋል፤

✓ መንግሰት ከሚመለከታቸው አካላት እና ከለጋሽ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት የቀለብ ፍጆታቸውን ጥራቱን ፣ መጠኑን እና ጊዜውን ጠብቆ እንዲያቀርብላቸው እንዲሁም የህክምና እና የትምህርት አገልግሎት እንዲያገኙ ተገቢውን ጥረት እንዲያደርግ፣

✓ መንግሰት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር የደህንነት ስጋት ያለባቸውን የተፈናቃይ ጣቢያዎች ደህንነቱ ወደተጠበቀበት ቦታ እንዲያዘዋውር፣

✓ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ተፈናቃዮች ያሉበት ሁኔታ ለኑሮ ምቹ ያልሆነ እና የሰብዓዊ እርዳታ አቅርቦት መጠን ከጊዜ ወደጊዜ እየቀነሰ የመጣና በቂ ትኩረት የሚፈልግ ጉዳይ በመሆኑ መንግስት በቂ ትኩረት በመስጠት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሚሆን የህግ ማእቀፍ በመዘርጋት እና የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ጉዳይ በቅርበት የሚከታተል እንዲሁም የህግ ማእቀፎቹን ተፈጻሚነት የሚከታተል እራሱን የቻለ ተቋም በማቋቋም ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራ፣

✓ በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች ታጥቀው የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች በካምፓላ ስምምነት አንቀጽ 7(5) ላይ በዝርዝር በተደነገገው መሰረት ዜጎችን በዘፈቀደ ከማፈናቀል እንዲቆጠቡ፣ ለዜጎች የሚሰጠውን ሰብዓዊ ድጋፍ እና ጥበቃ ከማደናቀፍ እንዲቆጠቡ፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን በነጻነት የመንቀሳቀስ መብት ከመገደብ እንዲቆጠቡ እና በዝርዝር በአንቀጹ ላይ ከተቀመጡ ድርጊቶች እንዲታቀቡ፣

✓ በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች በተነሱ ግጭቶች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው የሚገኙ ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች በዋናነት (ሴቶች፣ ህጻናት እና የአካል ጉዳተኞች) የካምፓላ ስምምነት እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሀገር ውስጥ መፈናቀልን በመሚመለከት ያወጣው የመመሪያ መርህ መንግስት ለእነዚህ ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች ሊሰጥ ይገባል ያሏቸውን ጥበቃዎች እና ድጋፎች በቂ ትኩረት በመስጠት እንዲያሟላ፣

✓ መንግስታዊ የሆኑ ተቋማት ከማዕከል ጀምሮ እስከ ቀበሌ ድረስ ያሉ አመራሮች ለመፈናቀል መነሻ ለሆኑ ግጭቶች ዘላቂ መፍትሄ በማፈላለግ በቁርጠኝነት በመስራት ለተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሄ (ወደመጡበት አካባቢ እንዲመለሱ፣ አዛው በሰፈሩበት ከማህበረቡ ጋር ተቀላቅለው እንዲኖሩ እና ወደ ሌላ ቦታ እንዲዘዋወሩ) በማበጀቱ ላይ የበኩላቸውን ሀላፊነት እንዲወጡ፣

✓የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህገመንግስት ለአንዳንድ የማህበረሰብ ክፍሎች የባለቤትነት መብትን የሰጠ ሲሆን ለሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች የባለቤትነት መብት የሰጠ አይደለም ይህም ችግሩን እንዳባባሰው ማወቅ ይቻላል ስለሆነም የክልል ህገ-መንግስቶች በሚወጡበት ጊዜ የፌደራል ህገ መንግስቱን በማይቃረን መልኩ መሆን እንዳለበት እሙን ነው ስለሆነም የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ2 መሻሻል የሚችልበት ሁኔታ ቢመቻች፣

✓ መንግስት ለተፈናቀሉ ሰዎች እውቅና በመስጠት ሌሎች የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ረጂ ድርጅቶች እርዳታ የሚያደርጉበትን መንገድ እንዲያመቻች፣ እነዚህም ረጂ ድርጅቶች የበኩላቸውን እንዲወጡ፣

✓ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ አባገዳዎች፣ የማህበረሰብ አንቂዎች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሄ (ወደ መጡበት አካባቢ እንዲመለሱ፣ አዛው በሰፈሩበት ከማህበረቡ ጋር ተቀላቅለው እንዲኖሩ እና ወደ ሌላ ቦታ እንዲዘዋወሩ) አግኝተው ከአከካባቢው ማህበረሰብ ጋር በሰላም የሚኖሩበትን ሁኔታ እንዲያመቻቹ

ኢሰመጉ ምክረ ሀሳቦችን ያቀርባል፡፡

በመጨረሻም ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የቆማችሁ ዜጎች፣ ሐገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማትም መንግሥት የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲያከብር፣ እንዲያስከብርና እንዲያሟላ ከዚህ በታች በተገለጹት አድራሻዎች በመጻፍና ስልክ በመደወል ጥያቄና ግፊት እንድታደርጉ ኢሰመጉ ይጠይቃል፡፡

• ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት
T.ሳ.ቁጥር ፡- 80001፣ ኢ-ሜል፡- national.parliament@ethionet.et፣ ፋክስ ፡- (+251) 011 155-0400፣የስልክ ቁጥር ፡- (+251) 011 124-1000፣
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

• ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት ለፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
T.ሳ.ቁጥር፡-20122/1000፣ኢ-ሜል ፡- kumashih@gmail.com
ፋክስ ፡- (+251) 011 124-1208/011 124-2308፣
የስልክ ቁጥር ፡- (+251) 011 122-3322፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

• ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፕሬዘዳንት ጽ/ቤት:-
T.ሳ.ቁጥር፡- 23698፣ ፋክስ ፡- (+251) 011 551- 8656፣
የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-8186፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

• ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት :- *T*.ሳ.ቁጥር፡-1031፣
ፋክስ፡- (+251) 011 122-6292፣
የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 124-1155፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

• የኢ.ፌ.ዲ.ሪፍትህ ሚኒስቴር ስልክ ቁጥር +251 115541868
ፋክስ +25115517775 ኢሜይል MOJMO@ETHIONET.ET
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
• ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሰላም ሚኒስቴር
T.ሳ.ቁጥር፡-5608፣ኢ-ሜል፡- mofatr1@yahoo.com፣
ፋክስ፡-(+251)011 551-1200፣
የስልክ ቁጥር፡-(+251) 011 515-3204፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

• ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም:
T.ሳ.ቁጥር፡-2459፣ኢ-ሜል፡ ombudsmaneth@ethionet.et፣
ፋክስ፡- (+251) 011 553-2073፣
የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 543-336፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

• ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን:
ፓ.ሳ.ቁጥር፡- 1165፣ ኢ-ሜ፡ hrcom@ethionet.et፣
ፋክስ፡ (+251) 011 550-4125፣
የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 550-4031፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

• ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴራል ፓሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀነራል ጽ/ቤት:
ፓ.ሳ.ቁጥር፡- 199፣ የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-2744፣
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

• ለኦሮሚያ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:
ፓ.ሳ.ቁጥር፡- 101769፣ ኢ-ሜል፡- oromiawiev@ethionet.et፣
ፋክስ፡- (+251) 011 551-3642 / (+251) 011 551-9633፣
የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 552-4247፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

• ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-
ፓ.ሳ.ቁጥር፡- 101769 ፋክስ፡- (+251) 011 552-4247
የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 555-0455 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

• ለአማራ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
ፓ.ሳ.ቁጥር፡- 1324፣ ፋክስ፡- (+251) 058 220-2511፣
የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-2659፣
ባሕርዳር፣ ኢትዮጵያ

• ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-
ፓ.ሳ.ቁጥር፡- 312 ፋክስ፡- (+251) 058 220-1068፣
የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-0924 / 058 220-0499
ባህር ዳር፣ ኢትዮጵያ

• ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
ፓ.ሳ.ቁ 44፣ ፋክስ፡- (+251) 057 775-0814፣
የስልክ ቁጥር፡- (+251) 055 77750109፣ አሶሳ፣ ኢትዮጵያ

• ለሐረሪ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
ፖ.ሳ.ቁጥር:-952 ፋክስ:-(+251)025 666 2530፣
የስልክ ቁጥር:- (+251) 025 666-1723 / 025 666-1746
ሐረር፣ ኢትዮጵያ

• ለሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-
ፖ.ሳ.ቁጥር:- 272 ፋክስ:- (+251) 025 666-0666፣
የስልክ ቁጥር:- (+251) 025 666-1799
ሐረር፣ ኢትዮጵያ

• ለአፋር ክልል ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
ስልክ ቁ. (+251) 0336660056
ሰመራ ኢትዮጵያ

• ለድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የከንቲባ ጽ/ቤት
የስልክ ቁጥር: (+251) 025 11 11 358 ፋክስ: (+251) 025 11 19 805

• ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የከንቲባ ጽ/ቤት
ስልክ.ቁ (+251) 0118591363
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ



የኢትዮጵያ
ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL (EHRCO)

Phone: (+251) 011 558-2387
E-mail: info@ehrco.org
Website: www.ehrco.org
Facebook: https://www.facebook.com/ehrco1/
Twitter: https://www.twitter.com/ehrcoethio
Telegram: https://t.me/ehrco